ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ

82ኛ ዓመት ቁጥር 157 የካቲት 7 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



# በስድስት ወራት ከ88 ሚሊዮን በላይ እንስሳት ክትባት ተሰጥቷቸዋል

**በዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ስድስት ወራት 90 ሚሊዮን ለሚጠጉ እንስሳት ድንበር ዘለልና ላልሆኑ በሽታዎች ክትባት መስጠቱን የግብርና ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት ጤናና ቬተርነሪ ፐብሊክ ሄልዝ መሪ ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር ውብሸት ዘውዴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ባለፉት ስድስት ወራት ከ70 ሚሊዮን በላይ እንስሳት የድንበር ዘለል በሽታዎችና 18 ሚሊዮን ድንበር ዘለል ያልሆኑ የእንስሳት በሽታዎች ክትባት ተሰጥቷል፡፡

ከ60 በመቶ በላይ የሰው ልጅ በሽታዎች የሚተላለፉት ከእንስሳት መሆኑን ዶክተር ውብሸት ገልጸው፤ እነዚህ በሽታዎች ወደ ሰው ተላልፈው ጉዳት እንዳያስከትሉ በማድረግ ረገድ ባለፉት ስድስት ወራት ከጎረቤት አገራት ወደ ኢትዮጵያ እንዲሁም ከአገር ውስጥ ወደ ውጭ የእንስሳት በሽታዎች እንዳይስፋፉ ለመከላከልም ከ88 ሚሊዮን በላይ እንስሳት ክትባት መስጠቱን ገልጸዋል፡፡

በስድስት ወራት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# የመሪዎች ጉባዔ

## ለከተማዋ የቱሪዝም ዘርፍ መነቃቃትን ይፈጥራል

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- በመዲናዋ በቅርቡ የሚካሄደው 36ኛው የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ጉባኤ ለአዲስ አበባ ከተማ ቱሪዝም መነቃቃት ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ፡፡

የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም መዳረሻ ልማትና ብቃት ማረጋገጥ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ አምደማርያም ማሞ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በከተማዋ ውስጥ የሚገኙ ለጉብኝት እና ለመዝናኛ የሚሆኑ ደረጃቸውን የጠበቁ የቱሪዝም መዳረሻዎች አሉ፡፡ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በማስተዋወቅ የቱሪዝም መነቃቃት ከመፍጠር ባለፈ ከፍተኛ የገቢ ምንጭ እንዲገኝ ያስችላል፡፡

አቶ አምደማርያም እንደተናገሩት፤ በከተማዋ

የመሪዎች ጉባዔ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል




ፎቶ - እዮብ ተፈሪ

# በክልሉ የሕዝብን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ የሕግ ማሻሻያ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው

**ጌትነት ተስፋማርያም**

ጅግጅጋ፡- በዘርፈ ብዙ ጉዳዮች የሕዝብን ተጠቃሚነት የሚያሳድጉ የተለያዩ የሕግ ማሻሻያዎችን እያደረግን ነው ሲሉ የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት ሙስጠፌ ሙሐመድ ገለጹ።

የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ስድስተኛ ዓመት አራተኛ መደበኛ ጉባኤውን ትናንት ማካሄድ ጀምሯል።

በክልሉ የሕዝብን ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል







አረንጓዴ አሻራ
GREEN LEGACY

# በአረንጓዴ አሻራ

## መርሃ-ግብር ከተተከሉት 25 ቢሊዮን ችግኞች 80 በመቶ ፀድቀዋል

**- በመጪው ክረምት 2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዷል**

**ማህሌት ብዙነህ**

አዲስ አበባ፡- ላለፉት አራት ዓመታት በአረንጓዴ አሻራ መርሃ-ግብር ከተተከሉት ከ25 ቢሊዮን ችግኞች 80 በመቶ የሚሆኑት መጽደቃቸውን የኢትዮጵያ ደን ልማት አስታወቀ፡፡

በኢትዮጵያ ደን ልማት የአነስተኛና ሰፋፊ ደን ልማት ዳይሬክቶሬት የደን ልማት ባለሙያ አቶ ዮናስ ክፍሌ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ ከ2011 ዓ.ም ጀምሮ በጠቅላይ ሚኒስትሩ መሪነት በአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ባለፉት አራት የክረምት ወራት የተካሄደው የችግኝ ተከላ ፕሮግራም ስኬታማ ነበር፡፡ ለመጪው

በአረንጓዴ አሻራ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል






## የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች

የነዳጅ ወጪን 50 በመቶ ይቀንሳሉ

ገጽ 3

# በኦሮሚያ ክልል በውሃ ፓምፖች ከሦስት መቶ 80 ሺህ ሄክታር በላይ ማልማት ተችሏል

## ከ15 ሺህ 400 በላይ የውሃ ፓምፖች ተሠራጭተዋል

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- በዘንድሮ ዓመት በኦሮሚያ ክልል በውሃ ፓምፖች በመታገዝ ከሦስት መቶ 80 ሺህ ሄክታር በላይ የእርሻ መሬት ማልማት መቻሉን የክልሉ መስኖና አርብቶ አደሮች ቢሮ ገለጸ።

የኦሮሚያ መስኖ እና አርብቶ አደሮች ቢሮ ኃላፊ ኢንጂነር ግርማ ረጋሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ባለፉት ዓመታት መንግሥት ከ28 ሺህ በላይ ፓምፖችን ማሰራጨቱን ተናግረው፤ በዘንድሮ ዓመት ከ15 ሺህ 400 በላይ ፓምፖች በኦሮሚያ ክልል እየተሰራጩ እንደሚገኙ አስታውቀዋል። በክልሉ ያለው የመስኖ እርሻ እንቅስቃሴ ጥሩ የሚባል መነቃቃት እንዳለውም ተናግረዋል።

ኢንጂነር ግርማ አክለውም በውሃ ፓምፖች በመታገዝ የእርሻ ሥራውን ከማካሄድ ጎን ለጎን በባህላዊ የመስኖ ልማት ከግማሽ ሚሊዮን ሄክታር በላይ የእርሻ መሬቶችን ማዳረስ እንደተቻለም አሳውቀዋል።

በመስኖ እርሻ ልማት ላይ በዋናነት የበጋ ስንዴ ቀዳሚውን ድርሻ እንደሚወስድ ያብራሩት ኃላፊው፤ ከበጋ ስንዴ ልማት ባሻገር በክልሉ የአትክልትና ፍራፍሬ ልማትም በመስኖ እየተካሄደ እንደሚገኝ አስረድተዋል። በክልሉ በመስኖ ከሚለሙ የፍራፍሬ ዓይነቶች ውስጥ አቮካዶ፣ ሙዝ እና ፓፓዬ እንደሚገኙበት ገልጸዋል።

በዚህም አቮካዶ ከ26 ሺህ ሄክታር በላይ፤ ሙዝ ከ26 ሺህ 800 ሄክታር በላይ እና ፓፓዬ ከ10 ሺህ ሄክታር በላይ በድምሩም 63 ሺህ ሄክታር የሚጠጋ በመስኖ እርሻ ፍራፍሬዎች ማልማት መቻሉን አስታውቀዋል።

በኦሮሚያ ክልል በፓምፖች የሚሠሩ የመስኖ እርሻ ሥራዎች በስልጠና እና ማኅበራትን በማደራጀት እንደሚሠሩ አብራርተዋል። በክልሉ የሚሰራጩ ፓምፖች በብድር እና በድጋፍ የተሰራጩ መሆናቸውንም የቢሮ ኃላፊው አስረድተዋል።



ኢንጂነር ግርማ ረጋሳ

በውሃ ፓምፖች የሚለማውን መሬት ጨምሮ ወንዞችን በመጥለፍና በባህላዊ መንገድ በሚሠሩ የመስኖ ሥራዎች የሚለማውን መሬት በዘንድሮ ዓመት አንድ ሚሊዮን ሄክታር ማዳረስ ተችሏል ነው ያሉት ኢንጂነሩ። ይህ ቁጥርም ከተያዘው ዕቅድ በላይ መሆኑን አመላክተዋል። የኅብረተሰቡ ፍላጎት ከፍተኛ መሆኑን ተናግረው፤ ተጨማሪ ፓምፖችንም ለማስገባት እየተሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል ከዚህ በፊት አገልግሎት በመስጠት ላይ የነበሩና በተለያዩ ምክንያቶች ተቋርጠው የነበሩ የውሃ ጉድጓዶችን በመጠገን ወደ ሥራ ማስገባት መቻላቸውንም ኢንጂነር ግርማ ተናግረዋል።

ከጥገና ጋር ተያይዞ ባለው የሰው ኃይል ጥገናዎች እየተካሄዱ መሆኑን በመጠቆምም በቀጣይም ተፈላጊውን የሰው ኃይል በማሰልጠን ወደ ሥራ የሚገባበት ሁኔታ እንደሚፈጠር አስረድተዋል። ወጣቶች ተደራጅተው የፓምፕ ጥገና ሥራውን እንዲያካሂዱ እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን አስታውቀዋል።

# በመዲናዋ በሴፍትኔት ፕሮግራም ከ530 ሺህ በላይ ዜጎች ተጠቃሚ ሆነዋል

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የሴፍትኔት ፕሮግራም ከተጀመረ ጀምሮ በሁለት ምዕራፎች ከ530 ሺህ በላይ ዜጎች ተጠቃሚ መሆናቸውን የከተማ አስተዳደሩ የሥራ ኢንተርፕራይዝ እና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ አስታወቀ። በሁለተኛው ምዕራፍ ከ130 ሺህ በላይ ዜጎች ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሥራ ኢንተርፕራይዝና ኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ የሥራ ዕድልና የምግብ ዋስትና ዘርፍ ኃላፊ አቶ ፍስሀ ጥበቡ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መርሃ-ግብሩ ከተጀመረ ጀምሮ በሁለት ምዕራፎች ከ530 ሺህ በላይ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል።

በመጀመሪያው ምዕራፍ 98 ሺህ አባወራዎች እና እማወራዎች በሥራቸው ከ400 ሺህ በላይ የቤተሰብ አባላት ተጠቃሚ መሆናቸውን የጠቆሙት ኃላፊው፤ በአምስት የአካባቢ ልማት ሥራዎች ላይ በተሰጣቸው ቀን እና ሰዓት መሠረት አካባቢያቸውን በማጽዳት፣ በማስዋብ እና ለከተማ ግብርና ምቹ ቦታዎችን በመፍጠር ገቢን እንዲያገኙ እና የምግብ ዋስትናቸውን ማረጋገጥ እንዲችሉ ተደርጓል ብለዋል።

እንደ አቶ ፍስሀ ገለጻ፣ ተሳታፊዎች ኑሯቸውን ሊያሻሽል የሚችል የሕይወት ክህሎት ስልጠና ተሰጥቷቸው ወደ መደበኛ ሥራ መቀላቀል ችለዋል። በተሰጣቸው ስልጠና መሠረትም ከ98 ሺህ አባወራዎች እና እማወራዎች መካከል 87 ሺህ የሚጠጉት በተለያዩ የሥራ መስኮች እንዲገቡ ተደርጎ የመጀመሪያው ምዕራፍ ተጠናቋል ብለዋል።

ሁለተኛው ምዕራፍ የሴፍትኔት መርሃ- ግብር በ32 ሺህ አባወራዎች እና እማወራዎች ተጀምሯል ያሉት ኃላፊው፤ በሥራቸው 109 ሺህ 918 የቤተሰብ አባላት ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ ብለዋል።

በዘንድሮው ዓመት 20 ሺህ 937 የቤተሰብ አባላት ተጨምረው በድምሩ ከ130 ሺህ የቤተሰብ አባላት በመርሃ-ግብሩ ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ ሲሉ አብራርተዋል። በአጠቃላይ በሁለቱም ምዕራፎች ከ530 ሺህ በላይ ዜጎችን ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል ነው ያሉት።

በሁለተኛው ምዕራፍም እየተሳተፉ የሚገኙትን ሰዎች ኑሯቸውን ለማሻሻል እና በተለያዩ ሥራዎች ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ በርካታ ሥራዎች እየተሠሩ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በአካባቢ ልማት ሥራዎች እንዲሳተፉ እና በሳምንት ሁለት ቀን የሕይወት ክህሎት ስልጠና እየተሰጣቸው ነው ብለዋል።

እንደ ኃላፊው ማብራሪያ፣ የሚሰጣቸው ስልጠና በሦስት የተከፈለ ሲሆን፤ የሕይወት ክህሎት ስልጠና፣ የፋይናንስ አያያዝና አጠቃቀም እና የራሳቸውን ሥራ እንዴት መፍጠር እንደሚችሉ ነው። በዚህም መሠረት በመንግሥት እና በግል ተቋማት ተወዳድረው መቀጠር እና የራሳቸውን ሥራ መፍጠር ይችላሉ ብለዋል።

የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ፕሮጀክቱን አጠናቀው ሲወጡ ከዓለም ባንክ በሚሰጣቸው እርዳታና ሠርተው በሚቆጥቡት ገንዘብ እንዲሁም በመንግሥት በሚመቻችላቸው ብድርና የመሥሪያ ቦታ አማካኝነት ከተረጂነት እንዲወጡ በማድረግ የራሳቸውን ሥራ ፈጥረው ኑሯቸውን እንዲያሻሽሉ ፕሮግራሙ ዕድል ፈጥሮላቸዋል።

ተጠቃሚዎች በአንድ ቤተሰብ በሳምንት አንድ ቀን አካባቢያቸውን እንዲያጸዱ በማድረግ ጽዱ እና ማራኪ መንደሮችን መፍጠር ተችሏል ብለዋል።

ዓለም ባንክ ባዘጋጀው የመመልመያ መስፈርት መሠረት በሁሉም ክፍለ ከተሞች ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ውስጥ የሚኖሩት የቅድሚያ ቅድሚያ እየተሰጣቸው በፕሮግራሙ ተጠቃሚ እየሆኑ ይገኛሉ። በዚህም በመጀመሪያው ምዕራፍ ከ400 ሺህ በላይ ሰዎች ተጠቃሚ ያደረገ ሲሆን፣ በሁለተኛው ምዕራፍ ደግሞ ከ130 ሺህ በላይ ሰዎች እየተሳተፉ እንደሆነ አቶ ፍሰሀ ተናግረዋል።

አቶ ፍስሀ እንዳሉት፤ በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ተጠቃሚዎቹ የጎደላቸው ነገር በተለያዩ ስልጠናዎች እንዲሟሉላቸው በማድረግ ኑሯቸውን ለማሻሻል በትኩረት ይሠራል ብለዋል።

# ዩኒቨርሲቲው በማኅበረሰብ አገልግሎት የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል እየሠራ ነው

**ታደሰ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ በሚሰጣቸው ማኅበረሰባዊ አገልግሎቶች የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል የሚረዱ ተግባራትን እያከናወነ መሆኑን ገለጸ።

የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የማኅበረሰብ ተሳትፎና ኢንተርፕራይዝ ልማት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶክተር ይስሀቅ የሱፍ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዩኒቨርሲቲው የትምህርት ጥራትን ለማምጣት በኦሮሚያ ክልል በሚገኙ ከቅድመ መደበኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ላይ ይገኛል።

ተቋሙ የትምህርት ጥራትን የተሻለ ለማድረግ አንድ ቦታ ብቻ መሥራት ውጤታማ ሊያደርግ እንደማይችል ተገንዝቦ የትምህርት ጥራት ችግርን ለመቅረፍ እና ጥራት ያለው ትምህርት ለማኅበረሰቡ ተደራሽ እንዲሆን በስፋት እየሠራ ነው ብለዋል።

የትምህርት ጥራትን ለማምጣት ከታች ጀምሮ ካሉ የትምህርት ደረጃዎች መሥራት አስፈላጊ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው በክልሉ የሙዓለ ሕፃናት የትምህርት አገልግሎት መስጠት ጀምሯልም ሲሉ አክለው ገልጸዋል።

በክልሉ በተመረጡ ሦስት ወረዳዎች ብቁ የሆኑ የሙዓለ ሕፃናት መምህራን ባለመኖራቸው ዩኒቨርሲቲው የሙዓለ ሕፃናት መምህራኑ ሞያቸውን የሚያጎለብትና ብቁ የሚያደርግ ስልጠና መስጠቱን የገለጹት ዶክተር ይስሀቅ፤ ለትምህርት አገልግሎት የሚያስፈልጉ የትምህርት ግብዓቶችን ለሦስቱ ወረዳዎች ድጋፍ ማድረጉን አስታውቀዋል።




ዶክተር ይስሀቅ የሱፍ

የትምህርት ጥራት ለማምጣት ለመምህራን ተጨማሪ ሥልጠናዎች በመስጠትና ለትምህርት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን የማሟላት ሥራ እየተሠራ መሆኑን የተናገሩት ዶክተሩ፤ ዩኒቨርሲቲው በክልሉ ለሚገኙ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዓመት እስከ 400 የሚሆኑ ወንበሮችና የተለያዩ የመማሪያ ቁሳቁሶችን በድጋፍ መልኩ ተደራሽ እያደረገ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

ዶክተሩ አክለውም ዩኒቨርሲቲው ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በመተባበር 500 ኮምፒዩተሮችን 20 ለሚሆኑ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተደራሽ ማድረጉንና በክልሉ በዲጂታል ቴክኖሎጂ ትምህርት እንዲሰጥና የዲጂታል ቴክኖሎጂ የትምህርት አሰጣጥን ተግባራዊ ለማድረግ ዩኒቨርሲቲው ከ20 ትምህርት ቤቶች ለተመረጡ መምህራን በዲጂታል ትምህርት ብቁ የሚያደርግ ሥልጠና የመስጠት እንቅስቃሴ ጀምሯል ብለዋል።

በአካባቢው ከፍተኛ ውጤት ያላቸውን ተማሪዎች በማወዳደር በዩኒቨርሲቲው ልዩ አዳሪ ትምህርት ቤት ገብተው የተሻለ ትምህርት እንዲያገኙ የማድረግ ሥራ መሥራቱን የገለፁት ምክትል ፕሬዚዳንቱ በትምህርት ጥራት ላይ በስፋት ላይ እየተሠራ መሆኑን አመላክተዋል።

# የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ወጪን 50 በመቶ ይቀንሳሉ

**በዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች የነዳጅ ወጪን 50 በመቶ እንደሚቀንሱ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ገለጸ፡፡ በመጀመሪያው ዓመት ኢትዮጵያ ከቻርጀር ጣቢያዎቹ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ እንደምታገኝበትም ተመላክቷል፡፡

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮርፖሬት ፕላኒንግ ሥራ አስፈፃሚ አንዷለም ሲአ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ኃይል የሚሞሉበት የቻርጅ ማድረጊያ ጣቢያ ትናንት በይፋ ሲጀመር እንደተናገሩት፤ ቻርጅ ማድረጊያ ጣቢያው በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች በነዳጅ ከሚሠሩት ተሽከርካሪዎች ለነዳጅ ከሚያወጡት ወጪ ጋር ሲነጻጸር እስከ 50 በመቶ ድረስ ቅናሽ ይኖራቸዋል፡፡

የትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር ዴኤታው አቶ በርኦ ሀሰን በበኩላቸው በመርሃ ግብሩ ላይ እንደገለጹት፤ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በአገር ውስጥ በማምረትና ከውጭ በማስመጣት እንዲሁም የቻርጅ መሙያ ማዕከል መሠረተ ልማት በመገንባት የሚሳተፉ ባለሀብቶችን በማበረታታት ወደ ተግባር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች በአንድ ጊዜ በአነስተኛ ወጪ በሚሞላ ባትሪ ከ200 እስከ 450 ኪሎ ሜትር መጓዝ ይችላሉ ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የጥገና እና መለዋወጫ ዋጋቸውም አነስተኛ ነው፣ ድምፅ



የማይበከሉ መሆናቸውና በሌሎችም መመዘኛዎች ነዳጅ ከሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች የበለጠ ተመራጭ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ሚኒስትር ዴኤታው፤ የኤሌክትሪክ ተሽከርካሪዎችን በስፋት ጥቅም ላይ በማዋል ከተሽከርካሪዎች የሚለቀቀውን በካይ ጋዝ ከመቀነስ ባሻገርም በርካታ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ይኖረዋልም ነው ያሉት፡፡

የካርዲናል ኢንዱስትሪያል ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ሥራ አስፈፃሚ ሊሊያ ኃይሉ በበኩላቸው በመጀመሪያው ዓመት 500 ቻርጅ ማድረጊያ ጣቢያዎች እንደሚገነቡም ተናግረዋል፡፡

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታዋ ሁሪያ አሊ በበኩላቸው የጣቢያዎቹ ሥራ መጀመር ኢትዮጵያ በቴክኖሎጂው ዘርፍ ለምታደርገው ጉዞ አዎንታዊ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ተናግረዋል፡፡

ቻርጅ ማድረጊያ ጣቢያው ለጊዜው የአዲስ አበባ ከተማ ላይ ትኩረቱን ሲያደርግ በሂደት ወደ ተለያዩ ክልሎች እንደሚስፋ እንዲሁም በመጀመሪያው ዓመት ኢትዮጵያ ከጣቢያዎቹ ከአንድ ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ እንደምታገኝበትም በመድረኩ ተመላክቷል፡፡

በኢትዮጵያ በቀጣይ 10 ዓመታት ውስጥ አምስት ሺህ የሚጠጉ አውቶቡሶችን እና 150 ሺህ ያህል የኤሌክትሪክ አውቶሞቢሎችን ጥቅም ላይ በማዋል የዘርፉን የኃይል ምንጭ ከነዳጅ ወደ ታዳሽ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማሸጋገር ሥራዎች መጀመራቸውም ተነግሯል፡፡

በኤሌክትሪክ ኃይል የሚሠሩ ተሽከርካሪዎች ቻርጅ ማድረጊያ ጣቢያው በትናንትናው ዕለት ይፋ ሲደረግ የውሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የሥራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል፡፡

# ማኅበራቱ ፍትሃዊ ግብይት እንዲሰፍን የድርሻቸውን እየተወጡ ነው

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በንግድ ሥርዓቱ ፍትሃዊነት ሰፍኖ ኅብረተሰቡ በሥርዓት እንዲገበያይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ያሉባቸውን ጫናዎች ተቋቁመው የድርሻቸውን እየተወጡ እንደሚገኙ የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ገለጸ፡፡

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ወይዘሮ ጫልቱ ታምሩ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከ22 ሺህ በላይ መሠረታዊ ኅብረት ሥራ ማኅበራት፣ 133 ዩኒየኖች እና ሁለት ፌዴሬሽኖች ተደራጅተው እየሠሩ ነው፡፡ አባል በማፍራት ደረጃም ወደ ሰባት ሚሊዮን የሚጠጋ አፍርተዋል፡፡

ማኅበራቱ 37 ሚሊዮን የሚጠጋ ቁጠባና ዕጣ ማሰባሰብ መቻላቸውን እና በ2014 ዓ.ም ብቻ ዘጠኝ ቢሊዮን ብር ለአባላት ብድር ማሰራጨታቸውንም የገለጹት ኃላፊዋ፤ በንግድ ሥርዓቱ ፍትሃዊነት ሰፍኖ ኅብረተሰቡ በሥርዓት እንዲገበያይ የኅብረት ሥራ ማህበራት ያሉባቸውን ጫናዎች ተቋቁመው የድርሻቸውን እየተወጡ እንደሚገኙ ጠቁመዋል፡፡

በተጨማሪም ማኅበራቱ ጠንካራ እንዲሆኑ ጊዜ፣ ገንዘብ እና ጉልበትን በአግባቡ በመምራት ውጤታማ ሥርዓት የመዘርጋት ግብ ተቀምጧል ሲሉ ገልጸዋል፡፡ እንደ ወይዘሮ ጫልቱ፤ ማኅበራቱ ከቀበሌ ስር ወጥተው ራሳቸውን ችለው የሚንቀሳቀሱበት ምህዳር እንዲፈጠር ይፈለጋል፡፡ አሠራራቸውን፣ አደረጃጀት እና አገልግሎት አሰጣጣቸውን እንዲያዘምኑና በቴክኖሎጂ የተደገፈ እንዲሆን በትኩረት ይሠራል፡፡

የምርት ማከማቻ፣ የፋይናንስ፣ የማኔጅመንት፣ የትራንስፖርት ችግር እና የተማረ የሰው ኃይል እጥረት ማኅበራቱ በሚፈለገው ደረጃ እንዳይደርሱ ተጽእኖ መፍጠሩንም ተናግረዋል፡፡ ይሁን እንጂ ማኅበራቱ ጫናውን ተቋቁመው የሕዝብን ችግር እየፈቱ ይገኛሉ ነው ያሉት፡፡

የኅብረት ሥራ ማህበራት የቁጠባ ባህል እንዲያድግ ጉልህ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ አባላቶቻቸው ቁጠባን ባህል እንዲያደርጉ በማስተባበር ጉልህ አስተዋጽኦ እያደረጉ



**ወይዘሮ ጫልቱ ታምሩ**

ይገኛሉም ሲሉ ነው ያመለከቱት፡፡

ማህበራቱን ከሸማቾች ጋር በማገናኘትም የምርት ትስስር የመፍጠር ሥራ እየተተገበረ እንደሚገኝ፣ በንግድ ሰንሰለቱ ውስጥ ያሉ ሕገወጥ ነጋዴዎችን ከሥርዓቱ በማስወጣት የንግድ ሥርዓቱ ፍትሃዊ እንዲሆን በማድረግም ሰፊ ሥራ መሠራቱንም አመልክተዋል፡፡

እንደኃላፊዋ ማብራሪያ፤ ኤግዚቢሽንና የቅዳሜ ገበያ በማዘጋጀት ሸማቾችና ነጋዴዎችን በማገናኘት የኅብረተሰቡ ችግር እንዲፈታና ገበያ እንዲረጋጋ እየተሠራ ነው፡፡

በአገር አቀፍ ደረጃ አርሶ አደሩ ለምርቱ ፍትሃዊ የምርት ዋጋ አላገኘም፡፡ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ከፌዴሬሽን አንስቶ፣ ከመሠረታዊ እስከ ዩኒየን አደረጃጀት እንዲዋቀር ምክንያት መሆኑንም ነው የገለጹት፡፡

ኮሚሽኑ ፍትሃዊነትን የማረጋገጥ፣ ሸማቾችን በማደራጀት እና ማህበራቱ ቴክኖሎጂን እንዲጠቀሙ በመደገፍ ቀልጣፋ የገበያ ሥርዓትን የማዘመን ሥራ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን ኃላፊዋ ገልፀዋል፡፡

# ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ ክምችትን ማሳደግ እና ገበያን ማረጋጋት ቀዳሚ ተግባሩ እንደሆነ ገለጸ

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- በመጪዎቹ ዓመታት የውጭ ምንዛሬ ክምችትን ማሳደግ እና ገበያን ማረጋጋት ቀዳሚ ተግባሩ እንደሚሆን ብሔራዊ ባንክ ገለጸ። ጤናማ ኢኮኖሚ ለመገንባት የምንዛሬ ማግኛ መንገዶችን የማስፋት፣ ተኪ ምርቶችን በአገር ውስጥ ማምረትና ባንኮች የሚሰጡትን ብድር የመገምገም ሥራ እየተተገበረ እንደሚገኝም አስታውቋል።

የብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ አቶ ሰለሞን ደስታ፤ ጤናማ ኢኮኖሚ ለመገንባት የውጭ ምንዛሪ ክምችትን ማሳደግ፣ ኢትዮጵያን ለውጭ ኢንቨስትመንት ምቹ ማድረግ እና የውጭ ንግድን ማስተዋወቅ አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የባንኮች የውጭ ምንዛሪ ክምችትን በማሳደግ ረገድ ብሔራዊ ባንክ የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳል ያሉት አቶ ሰለሞን፤ ከአገልግሎት ዘርፍ በተጨማሪ ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋትና የውጭ ምንዛሪ ክምችትን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ አቅም አለ ብለዋል።

የፋይናንስ ዘርፉን መንከባከብ እና ተደራሽነቱን ማስፋት አስፈላጊ እንደሆነ ገልጸው፤ ብሔራዊ ባንክ በመጪዎቹ ዓመታት የውጭ ምንዛሬ ክምችትን ማሳደግ እና ገበያን ማረጋጋት ቀዳሚ ተግባሩ እንደሚሆንም ጠቀመዋል፡፡

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ጤናማ ኢኮኖሚ ለመገንባት የውጭ ምንዛሬ ክምችትን ማሳደግና ገበያን ማረጋጋት ወሳኝ ነው። ለዚህም ብሔራዊ ባንክ በመጪዎቹ ዓመታት ጤናማ ኢኮኖሚ ለመገንባት ትኩረት አድርጎ ይሠራል ነው ያሉት፡፡

ባንኩ በጤናማ ኢኮኖሚ ውስጥ ያለውን ሚና የተገነዘበው ሲሆን የፋይናንስ ሴክተሩን በመንከባከብ እና የዘርፉን ተደራሽነት ለማስፋት ከፍተኛ ተሳትፎ አድርጓል። የኢትዮጵያ የፋይናንስ ዘርፉ ተደራሽነት ከጎረቤት አገራት ጋር ሲነጻጸር የኢትዮጵያ አጥጋቢ አይደለም ብለዋል።

ምክትል ገዢው አያይዘውም፤ ብሔራዊ ባንክ



**አቶ ሰለሞን ደስታ፤**

የአነስተኛ አርሶ አደሮችን ብድርና የፋይናንስ ተደራሽነት ለማሳደግ ከፍተኛ ርብርብ ማድረጉን እና ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ተቀናጅቶ እየሠራ መሆኑን አስረድተው፤ የኅብረተሰቡን የቁጠባ ባህል በማሳደግ ረገድ የባንኮችን አፈፃፀም ለማሻሻል በርካታ ሥራዎችን ሲሠራ እንደቆየና ይህንንም አጠናክሮ እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

በአፍሪካ ደረጃ የኢትዮጵያ የባንክ ኢንዱስትሪ በተደራሽነት እና በቴክኖሎጂ ዘልቆ በሚፈለገው ደረጃ ላይ እንዳልደረሰ ገልጸው፤ ሁኔታው በአካባቢው ያሉ ሁሉም ተዋናዮች ተሳትፎ ያስፈልገዋል ብለዋል። በዚህም መሠረት የባንክ ዘርፉን በቴክኖሎጂና በሰለጠነ የሰው ኃይል በማስታጠቅ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪነትን የሚያጎለብት ተግባር እንደሚያከናውን ምክትል ገዢው ተናግረዋል።

ወረታ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ኃ/የተ/የግ/ማ
Wereta International Business PLC

# ለከባድ ተሽከርካሪ ጎማ ተጠቃሚዎች

ድርጅታችን ወረታ ኢንተርናሽናል ቢዝነስ ኃላ.የተ.የግ.ማህበር ከተሰማራባቸው የሥራ ዘርፎች አንዱ የተለያየ መጠን ያላቸውን ጐማዎች ወደ ሀገር ውስጥ በማስገባት ለሽያጭ ማቅረብ ነው፡፡ በአሁኑም ወቅት ለሀገራችን መልክዓ ምድር ተስማሚ የሆነ ( TECHKING ) የተባለውን የጐማ ዓይነት በተለያየ መጠን (Size) እና ብዛት አስመጥቶ ለተጠቃሚዎች አቅርቧል፡፡

## የከባድ ጭነት ተሽከርካሪ ጎማዎች

- 12:00R20 22PR( የፊት)
- 12:00R20 22PR (የኋላ)
- 315/80R22.5 20PR (የፊትና የኋላ)

## የእርሻ ትራክተር ጎማዎች

- 14.9-24
- 12.4-24
- 14.9-30




**ይምጡና ይጐብኙን**
**በምርቶቻችን ጥራት ይረካሉ**




**አድራሻ፡- ዋና መ/ቤት ቦሌ መድሐኒዓለም ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ነው ብራይት ታወር ህንፃ 3ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 301-307**
☎ 0116-57 67 67 0116-63 00 20

0903-30 30 30, 0966-41 59 13, 0940-06 85 75
**የሽያጭ ማዕከል፡ ቃሊቲ ሸዋ ዳቦ አካባቢ**
0911 02 08 50

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስቃል መታመንን ያሳየው የስንዴ ኤክስፖርት!

የለውጥ ኃይሉ ወደ ሥልጣን ከመጣበት ማግስት ጀምሮ በተጠናና በተቀናጀ መንገድ ሀገርን ከነበረችበት ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ችግሮች ለመታደግ የሚያስችሉ ሰፋፊ ሥራዎችን ሠርቷል ፤እየሠራም ነው። በዚህም እየተገኘ ያለው ውጤት ከፍ ያለ ፣ እንደ ሀገር የጀመርነው የለውጥ/የብልጽግና ጎዳና ተስፋ ሰጭ እንደሆነ ያመላከተ ነው።

በተለይም ለውጡ በተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጪ ኃይሎች የተናበበ ተግዳሮት/ፈተና እየተናጠ ባለበት ሁኔታ፤ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከነበረበት ችግር ታድጎ ወደ አዲስ የስኬት ምዕራፍ እንዲሻገር እያሳየ ያለው ቁርጠኝነትና ከዚህ የሚመነጨው ውጤታማነቱ፤ ሃገርን በመታደግ ሂደት ትልቅ አቅም እየሆነ ነው።

በተለይም ቀደም ሲል የተጀመሩ ሃገር አቀፍ ትላልቅ ፕሮጀክቶች /እንደ ዓባይ ግድብ ያሉ/ አጋጥሟቸው የነበሩ ችግሮችን በማጥናት፤ በቂ በጀት በመመደብ ፤ጠንካራ ክትትል በማድረግ ፕሮጀክቶቹ ነፍስ ዘርተው በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ማበርከት እንዲችሉ እየተሠራና ውጤት እየተገኘበት ነው። አንዳንዶቹም ፍጹም ከመዘረፍ አደጋ ወጥተው በአዲስ አደረጃጀትና ተልዕኮ ሃገርንና ሕዝብን በሚጠቅሙበት ቁመና ላይ እንዲገኙ አድርጓል።

አዳዲስ ትላልቅ ሃገራዊ ፕሮጀክቶችን/ የኢትዮ-ቻይና የወዳጅነት ፓርክ ፣ የእንጦጦ ፓርክ፣ የአንድነት ፓርክ /በአጭር ጊዜ አቅዶ በማጠናቀቅ ፤በፕሮጀክት አፈጻጸም አዲስ ታሪክ ማስመዝገብ ችሏል። ለለውጥ ራሱን እንዳስገዛ መንግሥትም ለሕዝብ በአደባባይ የገባቸውን ቃሎች በመተግበር፤ ለቃሉና ለሕዝብ ያለውን ከበሬታ በተጨባጭ አሳይቷል።

በከፍተኛ የመንግሥት ክትትል እየተገነቡ ያሉ የኮይሻ፣ የወንጪ እና የጎርጎራ ፕሮጀክቶች ሀገሪቱ ያላትን የተፈጥሮ መስሕቦች በማልማት ተጨማሪ ሀገራዊ የኢኮኖሚ አቅም ለመፍጠር የሚደረጉ ጥረቶች፤ በአንድም ይሁን በሌላ ሀገርን ወደ ብልጽግና ለማሻገር በመንግሥት የሚደረጉ ጥረቶች እርሾ ተደርገው የሚወሰዱ ናቸው።

ከዚህም ባለፈ ሃገሪቱ በስንዴ ምርት ራሷን ችላ፤ ምርቱን ወደ ውጪ በመላክ የውጪ ምንዛሪ እንድታገኝ ከፍ ባለ ትኩረት ሲሠራ ቆይቷል። በዚህም ስኬታማ በመሆን ከትናንት በስቲያ ሃገሪቱ ስንዴ ወደ ውጪ ኤክስፖርት ማድረግ ጀምራለች። ይህ ታሪካዊ እውነታ በሃገሪቱ የተጀመረው ለውጥ በብዙ ፈተናዎች ውስጥም ቢሆን እያስመዘገበ ያለው ውጤት ከችግሮች በላይ የመብረር አቅም እየጎለበተ መምጣቱን ያመላከተ ሆኗል።

የለውጥ ኃይሉ ለሕዝብ ቃል በገባባቸው ጉዳዮች ዙሪያ የቱን ያህል በትጋት እየሠራ እንደሚገኝ፤ ይህ ትጋቱ ከሚያጋጥሙ ፈተናዎች በላይ አድርጎ አፉን ሞልቶ በድፍረት በአደባባይ እንዲናገር ፤በሀገራዊ የታሪክ መዝገብም የአዲስ ታሪክ ባለቤት እያደረገው እንደመጣ በተጨባጭ ያሳየ ነው። ለሃገራዊ ነገዎች ብሩህነትም እንደ አንድ ማሳያነት ሊጠቀስ የሚችል ነው።

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጉዳዩን አስመልክተው በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው፤የስንዴ ኤክስፖርት መጀመሩን አስመልክተው ባስተላለፉት መልዕክት “እኛ የምናልም፣ ያለምነውን የምንናገር፣ የተናገርነውን ሌት ከቀን የምንሠራ፣ የሠራነውን ደግሞ አጠናቅቀን የምናሳይ ስለመሆናችን ማረጋገጫ ነው” ማለታቸውም ለዚህ ነው። ለቃላቸው ከሁሉም በላይ ምስክር ሊሆን የሚችለውም የተሠራው/ የሚታየው ሥራ ብቻ ነው።

የለውጥ ኃይሉን በተለያዩ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ችግሮች ፋታ በመንሳት ለሕዝብ የገባቸው ቃሎቹ እውን እንዳይሆኑ የሚደረጉ ጥረቶች ቀን ተቀን መልካቸውን እየቀየሩ ሃገራዊ ፈተና እየሆኑ ባሉበት ሁኔታ እንዲህ ዓይነት ሀገራዊ ስኬቶችን ማስመዝገብ በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

ይህ የመንግሥት ሀገራዊ ጥረት ከዚህ ከፍ ባለ ደረጃ ተግባራዊ ሆኖ ለማየት መላው ሕዝባችን፤ከእያንዳንዱ ሀገራዊ የብጥብጥ አጀንዳ በስተጀርባ ያለውን ስውር አጀንዳ/ለውጡን ተስፋ አልባ ማድረግና ማደናቀፍ መሆኑን በአግባቡ ተገንዝቦ ዓይኖቹን ከለውጡ አጁንዳዎች ላይ ሳያነሳ ከለውጡ ኃይል ጋር በቁርጠኝነት ሊሰለፍ ይገባል። በዚህም ለከራሱ አልፎ መጪውን ትውልድ የተሻለ ሀገር ባለቤት እንዲሆን ማድረግ ይችላል!


## አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

## የተጀመረውን የሰው ተኮር ልማት ለማስቀጠል

ታዝበው ዘመኑ

አንድን አገር ለማስተዳደር ውክልና የወሰደ መንግሥት ከሚጠበቅበት ጉዳዮች መካከል ዋነኛው ተጠቃሽ የሆነው የሕዝብን ሰላም ማስጠበቅና ኅብረተሰቡን በልማት ተጠቃሚ ማድረግ ነው። ኅብረተሰቡን በልማት ተጠቃሚ ለማድረግ ደግሞ ራሱ ኅብረተሰቡን ያሳተፈ ተግባር ማካሄድ ዋንኛ ተመራጭ ጉዳይ ነው።

ከዚህ ዓይነት እንቅስቃሴ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን በአዲስ አበባ ከተማ በስፋት እየተካሄዱ ያሉ ሰው ተኮር የልማት ሥራዎችን ለዛሬ ማንሳት ወደድኩ። በቅድሚያ በቤት ግንባታ ዙሪያ ያለውን እንመልከት። የፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት በቤት ተደራሽነት ዙሪያ ያስጠናው ጥናት እንደሚያመለክተው፤ ቤትን ለዜጋ ተደራሽ ለማድረግ የሚደረገው ጥረት በግንባታ እቃዎች አቅርቦት የዋጋ ንረት ምክንያት ፈተና ውስጥ ወድቋል ።

ከዚህ የተነሳም ዜጎች ደረጃውን ባልጠበቀ ቤት ውስጥ እየኖሩ ከምግብና ሌሎች ፍላጎቶች ቀንሰው ከገቢያቸው 30 በመቶ በላይ ለቤት ኪራይ የሚከፍሉ ቁጥራቸው ከፍተኛ እየሆነ ነው። አሁን ባለው ሁኔታ ቤት መግዛት የማይታሰብ እስከመሆን ደርሷል። ቤት መግዛት ቀርቶ የአነስተኛው የስቱዲዮ ቤት የኪራይ ዋጋም ለአብዛኛው ሠራተኛ የሚቻል አይደለም።

መንግሥትም ለዚህ ጉዳይ እልባት ለመስጠት የቤት ግንባታ ፕሮጀክቶች ነድፎ እየተንቀሳቀሰ ነው። አቅም ላላቸው ለነዋሪዎችም መሬት በዝቅተኛ ዋጋ በሊዝ በማከራየት የራሳቸውን መኖሪያ ቤቶች እንዲገነቡ እያገዘ ነው። ከዚህም አልፎ የመንግሥት ተቋማትና ባለሀብቶችን በማሰለፍ የአቅመ ደካሞችን ቤት በማደስ ላይ ይገኛል ።

የቤት ማደስ ሥራው ትኩረት ተሰጥቶት በሁሉም ክፍለ ከተማዎች በሚባል መልኩ በተገጣጣሚ ቤቶች እየተሠራ እንደሆነ ይታወቃል። ፕሮጀክቶቹን ከግብ ለማድረስም በከተማ አስተዳደሩ አመራሮች ጠንካራ ክትትል እየተደረገ ይገኛል።

ከፕሮጀክቶቹ ብዙ ትምህርት እየተወሰደ ሲሆን፣ ቁርጠኝነት ካለ ፕሮጀክቶችን በተያዘላቸው ጊዜ ማጠናቀቅ እንደሚቻል በማሳያነት እየተጠቀሱም ነው። በቀጣይም በሚኖሩ የግንባታ ሥራዎች የከተማውን ውበትና ደረጃ በጠበቀ መልኩ ግንባታዎች እንደሚቀጥሉም እየተነገረ ነው ። ይህ ለከተማዋ ነዋሪዎች በተለይም ለአቅመ ደካሞች ትልቅ እፎይታ ሆኗል ።

በከተማ እየተከናወኑ ካሉ ሰው ተኮር የልማት ሥራዎች ሌላኛው የመስቀል አደባባይ ፕሮጀክት ነው። ፕሮጀክቱ የቀድሞ ይዘቱን ሳይቀይር ከዚህ ቀደም ሲሰጥ የነበረውን ሃይማኖታዊ ፣ሕዝባዊ እና ሌሎች ማኅበራዊ ዝግጅቶች በተሻለ እና ምቹ በሆነ መልኩ ለመስጠት በሚያስችል መልኩ ተገንብቷል።

ፕሮጀክቱ በአካባቢው የሚስተዋለውን የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራ ጥበትን ከመቅረፍ አንጻር እስከ አንድ ሺህ 400 የሚደርሱ ተሽከርካሪዎችን የሚያስቆሙ ባለሁለት ወለል የመኪና ማቆሚያ ያለው ነው። በተጨማሪነት 35 ሱቆች፣ 140 መፀዳጃና 20 መታጠቢያ ቤቶችም አሉት።

ለቢሮ መገልገያ ክፍሎች፣ ዘመናዊ አሳንሳሮች (ሊፍቶች)፣ ለ24 ሰዓት አገልግሎት የሚሰጡ የደህንነት ካሜራዎች፣ ዘመናዊ ዲጂታል ስክሪኖች እና የእሳት መከላከያ አለው። ሱቆቹ የኢትዮጵያን ባህል እና ቅርሶች የሚያሳዩ እና ለጎብኚዎች ለመሸጥ በሚያመች መልኩ የተገነቡ ናቸው። በአደባባዩም ነጻ የዋይ.ፋይ (WiFI) ኢንተርኔት አገልግሎት ይሰጣል።

ሌላው ደግሞ በቅርቡ የሚገነባው በለሚ ኩራ ክፍለ ከተማ የሚገኘው ለሚ ፕሮጀክት ነው። ፕሮጀክቶች በመሐል ከተማ ብቻ ሳይሆን በዳር አካባቢዎችም ማዳረስን ታሳቢ ያደረጉ እንደሆነም ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽሕፈት ቤት የተገኘው መረጃ ያሳያል። እንደመረጃው ከሆነ ግንባታው በአንድ ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ብር በጀት የሚገነባ ነው።

አዲስ አፍሪካ ኮንቬንሽን ሴንተር ታሳቢ በማድረግ በዓለም አቀፍ ስብሰባዎችና ኤግዚቢሽኖች በማስተናገድ ለአካባቢው ተያያዥነት ያለው ጠቀሜታ እንዲኖረው ታስቦ የተገነባ ማዕከል ነው። አካባቢውንም በማስዋብ ከመንገድ አካፋዮች፣ አደባባዮችንና የእግረኛ መንገዶች ጋር ተናቦ የሚሠራ ሲሆን፣ 14ሺህ 400 ካሬ ሜትር ቦታ ላይ የሚያርፍ ፕሮጀክት ነው።

ፕሮጀክቱ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ አጋርነት ከጥበብ ዲዛይንና ቢዩልዲንግ ፒ.ኤል.ሲ ጋር በመተባበር በ10 ወራት ተገንብቶ የሚጠናቀቅ ነው። ይህ ፕሮጀክት የስብሰባ አዳራሽ፣የሕዝብ መሰባሰቢያ ስፍራ (public space)፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ (gym) ፣ የሠርግና ለሌሎች አገልግሎቶች የሚውል መናፈሻ፣ የመኪና ማቆሚያ፣ ሱፐርማርኬት ፣ የቢሮ አገልግሎት የሚሰጡ ቦታዎች ፣ የማንበቢያ ስፍራ እና የመሳሰሉት የሚገኙበት ነው።

ይህ ፕሮጀክት በግንባታው ወቅት እስከ 1 ሺህ 100 ያህል ዜጎች የሥራ እድል የሚፈጥር ሲሆን፣ በቀጣይ በቋሚነት ለ400 ዜጎቻችን የሥራ እድል የሚፈጥር ይሆናል። ከነዚህ በተጨማሪም በከተማዋ ተገንብተው ወደ ሥራ የገቡ የኢትዮ- ቻይና ወዳጅነት ፓርክ፣ አንድነት ፓርክን መጥቀስ ይቻላል ።

በአጠቃላይ በአዲስ አበባ እየተካሄደ ያለው ሰው ተኮር የልማት እንቅስቃሴ የሚበረታታ፤ እውቅና የሚሰጠው ነው።

በእርግጥ የሰው ተኮር የልማት ፕሮጀክቶች በማለት ማሳያ የሚሆኑትን ለማንሳት ወደድኩ እንጂ ሌሎችም በተለያዩ ክፍለ ከተማዎች የተሠሩ ስለመኖራቸው ከመዲናዋ ነዋሪዎች የተሰወረ አይደለም። ከእነዚህም መካከል የከተማ ግብርና፣ የአረጋውያን የምገባ ማዕከላት፣ የሸገር ዳቦ መሸጫ ማዕከሎች እና ሌሎችም ፕሮጀክቶች ተጠቃሽ ናቸው።

በእርግጥ እነዚህ የተጠቀሱት የሰው ተኮር ፕሮጀክቶች በቂ ናቸው የሚል አተያይ የለኝም፤ አይኖረኝምም። እንደሚታወቀው አዲስ አበባ የኢትዮጵያውያን ብቻ ሳትሆን የአፍሪካውያንም መዲና ናት። ከዚህ አንጻር ሲታይ ከዚህም በላይ ሰው ተኮር ልማት እንደሚያስፈልጋት እሙን ነው። ስለዚህም የተጀመረውን ሰው ተኮር ልማት አጠናክሮ ማስቀጠል ያስፈልጋል። ለዚህ ደግሞ የባለድርሻ አካላት ብሎም የነዋሪውም ቀና አመለካከት የግድ ይላል።

# የበልግ ዝናብ ዘግይቶ መግባቱ የመስኖ ሰብሎችን ለመሰብሰብ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- ለጥቂት ቀናት ዘግይቶ የሚገባው የዘንድሮ በልግ ዝናብ በመስኖ የተዘሩ ሰብሎችን ለመሰብሰብ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል ሲል ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር መለስ መኮንን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት ይፋ የተደረገው የዘንድሮው የበልግ ዝናብ መዘግየት የመስኖ ሰብሎችን ለመሰብሰብ ምቹ አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡

በበልግ ወቅት በሰሜን፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ ምሥራቅ፣ ደቡብ፣ ደቡብና ደቡብ ምዕራብ የአገሪቱ ክፍሎች ሰብሎች በስፋት የሚመረቱበት ወቅት ነው ያሉት ዶክተር መለስ፤ ከዚህም አንጻር ሰሜን፣ ሰሜን ምሥራቅ እና ምሥራቅ ከ 5 እስከ 30 በመቶ፣ ደቡብ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ደግሞ ከ30 እስከ 60 በመቶ የአጠቃላይ የምርት ድርሻ አላቸው ብለዋል፡፡

ለእነዚህ አካባቢዎች ኢትዮጵያ ሜትሮሎጂ ኢንስቲትዩት አካባቢያዊ የዝናብ ክስተቶችን መሠረት በማድረግ የ2015 ዓ.ም የበልግ ወቅት ዝናብ ስርጭት ከመደበኛው ጊዜ ትንሽ ዘግይቶ እንደሚጀምር መተንበዩንና በአጠቃላይ የዝናብ ስርጭቱ ዘግይቶ የሚጀምር ቢሆንም ከመደበኛ የዝናብ ስርጭት ጋር ተቀራራቢ ሆኖ ሲወጣም በመደበኛ ጊዜው እንደሚወጣ አክለው ገልጸዋል፡፡



ፎቶ ገባቦ ገብሬ

**የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር መለስ መኮንን**

ሚኒስትር ዴኤታው፣ ሰሜን በከፊል፣ ሰሜን ምሥራቅ፣መካከለኛ እና ምዕራብ የአገሪቱ አጋማሽ ክፍሎች በሚያዝያ እና በግንቦት ወራት የተሻለ ዝናብ ስለሚኖራቸው በሚያዝያና ግንቦት ወራት ለሚዘሩ ሰብሎች በተለይ እንደ ማሽላና በቆሎ ዓይነቶች ለእርሻ ዝግጅት እና ለአዝመራ ወቅት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑን አክለው አብራርተዋል፡፡ በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች ለመኸር የሚደረገውን እርሻ ዝግጅት የማመቻቸች ዕድል አለው ብለዋል፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ይህንን ትንቢያውን መሠረት በማድረግ የተለያዩ አሠራሮችን ለመጠቀም ጥረት እያደረገ ነው ያሉት ዶክተር መለስ፤ በእነዚህ አካባቢዎች ለሚዘሩ ሰብሎች በተለይ በመስኖ እንዲታገዙ በማድረግ የእንስሳት መኖ ለማምረት ብሎም የመጠጥ ውሃ ለማቅረብ በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል፡፡

ለበልግ እርሻ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ለአርሶ አደሩ ወቅቱን ጠብቆ እንዲደርስም እየተሠራ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የዝናብ እጥረት በሚስተዋልባቸው አካባቢዎች የተዘሩ ሰብሎች የተለያዩ ውሃ ማጠራቀሚያ ዘዴዎችን ሥራ ላይ ለማዋል ይሠራል ብለዋል፡፡

እንደ ዶክተር መለስ ማብራሪያ፤፣ ለአርሶ አደሩ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በማቅረብ በተወሰነ ርጥበት ቶሎ ሊደርሱ የሚችሉ ሰብሎችና አትክልት ዝርያዎችን እንዲጠቀሙ ይደረጋል፡፡

ዝናብ እጥረት ሲከሰት ሙቀት ይጭምራል ያሉት ዶክተር መለስ፤ ሙቀት ከጨመረ ደግሞ ሰብሎችን የሚጎዱ ተባዮች ስለሚከሰቱ ተባዮቹን አሰሳ በማድረግ ማጥፋት የሚያስችሉ ኬሚካሎች እና ሌሎች መከላከያ ዘዴዎችን የመጠቀም ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል፡፡

ለበልግ ወቅት አምራቾች ምክረ ሀሳብ ተዘጋጅቶ እንዲደርሳቸው እየተደረገ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ በየደረጃው የሚገኙ ባለሙያ እና አርሶ አደሩ በቅድመ ትንቢያ መሠረት የተሰጡ ምክረ ሀሳቦች ከአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናኘት እንዲጠቀሙና ተገቢው ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ጠይቀዋል፡፡

በበልግ ወቅት በየዓመቱ እስከ 2 ሚሊዮን ሄክታር በዘር እንደሚሸፈን ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

# በአረንጓዴ አሻራ መርሃ-ግብር ከተተከሉት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ክረምት ወቅትም ሰፊ ዝግጅት እየተደረገ ነው።

በመርሃ ግብሩ ላይ በፌዴራል ደረጃ ከግብርና ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ደን ልማት፣ ከውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣ ከከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር እንዲሁም ከተለያዩ ክልሎች የተውጣጡ ኮሚቴዎችን በማቋቋም 20 ሚሊዮን ዜጎች እንደተሳተፉበት አቶ ዮናስ አክለው ተናግረዋል።

እንደ ተቋም ለተተከሉት ችግኞች እንክብካቤ ከማድረግ ባለፈ የተከለው አካል በባለቤትነት ኃላፊነት ወስዶ አጥር ከማጠር ጀምሮ፣ የማረምና የመኮትኮት፣ ውሃ የማጠጣት እና የመሳሰሉት የእንክብካቤ እና የክትትል ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ አቶ ዮናስ ተናግረዋል።

ይህ መርሀ ግብር ለበርካታ ዜጎች የሥራ ዕድል ከመፍጠር ባለፈ ዓለምን እያሳሰበ ያለውን የዓለም ሙቀት መጨመር ለመቀነስ፣ የአፈር መሸርሸርን ከመከላከልና የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ በዘለለ ለኢኮኖሚያዊ ዕድገቱ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው አቶ ዮናስ አክለው አብራርተዋል።

አቶ ዮናስ እንደገለጹት፣ በ2014 ዓ.ም የመጀመሪያ ስድስት ወራት ዝግጅት 227 ሚሊዮን ችግኞችን ማፍላት የተቻለ ሲሆን በዘንድሮ መርሃ-ግብር ላለፉት ስድስት ወራት 348 ሚሊዮን ችግኞችን ማፍላት መቻሉንና ይህም ካለፈው ተመሳሳይ ጊዜ በ53 ነጥብ 4 በመቶ ብልጫ አሳይቷል።

የበጀት እጥረት፣ የአተካከል ችግር፣ ሕዝቡን በተገቢው አለማደራጀት፣ ሙሉ አቅምን ያለመጠቀም፣ ከተተከለ በኋላ ወጥ በሆነ መልኩ እንክብካቤ ያለማድረግ እና ልቅ ግጦሽ የመርሃ-ግብሩ ተግዳሮቶች ናቸው ያሉት ባለሙያው፤ በቀጣዩ መርሃ-ግብር ያሉትን ጉድለቶች ለመፍታት በትኩረት ለመሥራት ታቅዷል ብለዋል።

ለዚህም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ባስቀመጡት አቅጣጫ 5ኛው ዙር የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር 2 ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኞችን በጥራት ለመትከል መታቀዱን ገልጸው፤ እነዚህም አንድ ቢሊዮን የደን ችግኝ እና 1 ነጥብ 5 ቢሊዮን የጥምር ደን ችግኞች መሆናቸውን ዘርዝረዋል።

የተዘጋጁት ችግኞች ለማገዶ፣ ለግንባታ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለአካባቢ ጥበቃ አገልግሎት ተብለው የተለዩ ሲሆን ችግኞቹም አገር በቀል እንደሚሆኑ ተናግረው፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኘው ይህ መርሀ ግብር ኅብረተሰቡ ችግኝ መትከልን የህልውናው ጉዳይ አድርጎ በትኩረት መሥራት ይጠበቅበታል ብለዋል።

# የመሪዎች ጉባዔ ለከተማዋ የቱሪዝም ዘርፍ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የመንግሥት፣ የሃይማኖት ተቋማት፣ እንዲሁም የግል የቱሪዝም መዳረሻ የሚሆኑ መስህቦች እንዳሉ ተናግረው፤ ከእነዚህ ውስጥ እንጦጦ ፓርክ፣ አንድነትፓርክ፣ ለተለያዩ መድረኮች የሚሆን የወዳጅነት ፓርክ፣ የሳይንስ ሙዚየም እንዲሁም እንጦጦ ሙዚየም በዋናነት ይጠቀሳሉ ብለዋል።

ጉባዔውን የተሳካ እና የማይረሳ ለማድረግ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩል ለሦስት ወራት ያህል ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅድመዝግጅት ሲደረግ መቆየቱን ገልጸው፤ እሳትና ድንገተኛ አደጋ ከመቆጣጠር፣ ጥሩ የኢንተርኔት አገልግሎት እንዲኖር፤ ሰላምን ጸጥታ እንዲጠበቅ እንዲሁም ጥሩ የሆቴል እና የግብይት አገልግሎት እንዲኖር የማድረግ ሥራ ተሠርቷል፤ ለዚህም አገልግሎት አሰጣጡ ምን መምሰል እንዳለበት እና ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ከክፍለ ከተማ ጀምሮ ኮሚቴ በማቋቋም የክትትል እና ድጋፍ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ አቶ አምደማርያም ተናግረዋል።

ከሆቴል አገልግሎት በኩል በከተማችን ከሚገኙ ከባለአንድ ኮከብ ሆቴሎች ጀምሮ እስከ ባለአምስት ኮከብ ሆቴሎች ባለቤቶችን በመሰብሰብ ቱሪስቶችን ተቀብሎ ለማስተናገድ የሚያስፈልጋቸውን ቅድመ ሁኔታዎች እንዲያመቻቹ መደረጉን ገልፀዋል።

ሆቴሎቹ ጥሩ እንግዳ አቀባበል እንዲኖር አራቱንም ቀናት የቡና ሥነሥርዓት በማዘጋጀት፣ አስተናጋጆች የባህል አልባሳት ለብሰው እንዲያስተናግዱ በማድረግ



ባህል ለማስተዋወቅ፣ ባህላዊ ቁሳቁሶች ሽያጭ እና ባህላዊ ሙዚቃ እና የባህል ምሽት ፕሮግራሞች ያዘጋጃሉ ብለዋል።

ጉባዔው የውጭ ምንዛሬ በማስገኘት የራሱን አስተዋፅዖ ከማበርከቱም በላይ የከተማዋን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ የሚያሳድግ ነው ያሉት አቶ አምደማርያም፤ የከተማዋን ገጽታ ከመገንባት አንጻር እንግዶች በሚተላለፉበት አካባቢዎች ላይ የቱሪስት ካርታዎች እንዲታዩ፣ አዲስ አበባ ያወጣችውን የቱሪዝም ብራንድ በሚታይ ቦታ በመለጠፍ፣ ከተማዋን ጽዱ በማድረግ፣ አዲስ አበባን ሊያስተዋውቁ የሚችሉ የተለያዩ በራሪ ወረቀቶችን የማስቀመጥ የቅድመ ዝግጅት ሥራ ተሠርቷል ብለዋል።

በዚህ ዓመት በፊት ከነበረው በተለየ ሁኔታ የአዲስ አበባን ብራንድ የማስተዋወቅ ሥራ እንዲሁም ከመንግሥት ባለድርሻ አካላት ባለፈ የተለያዩ የግል ተቋማት ጋር በጋራ በመሆን የራሳቸውን አሻራ እንዲጥሉ በጋራ እየሠራን ነው ብለዋል።

# በክልሉ የሕዝብን...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በጉባኤው የተገኙት የክልሉ ፕሬዚዳንት ሙስጠፌ ሙሐመድ እንደገለጹት፤ የኅብረተሰቡን ተጠቃሚነት የሚያሳድጉ የተለያዩ የሕግ ማዕቀፎች በማዘጋጀትና ያሉትንም በማሻሻል ረገድ ተጨባጭ ውጤቶች ተገኝተዋል።

የክልሉ ሥራ አስፈጻሚ ካቢኔ ከኢነርጂ፣ ውሃና ፍሳሽ፣ ከፋይናንስ አሠራር ሂደቶችና ከሲቪል ማህበራት እንዲሁም ከተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ የሕግ ማሻሻያዎች ላይ ግብዓት የማከል እንዲሁም ውሳኔ የማስተላለፍ ኃላፊነቱን ሲወጣ መቆየቱን አቶ ሙስጠፌ አስታውቀዋል።

በሶማሌ ክልል የከተማና የገጠር ውሃና ፍሳሽ ሥራዎችን በተቀናጀና የየአካባቢውን ሁኔታ መሠረት ባደረገ አግባብ ለመምራት የሚያስችል የአዋጅ ማሻሻያ መደረጉንም ገልጸዋል።

በሌላ በኩል የክልሉን ኢነርጂና ማዕድን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀምና የሕዝቡን ሁለንተናዊ ዕድገት ለማጠናከር የሚያግዙ የሕግ ማሻሻያዎች ላይ ያተኮሩ ሥራዎች ተከናውነዋልም ብለዋል።

የሕግ ማሻሻያዎቹ ከኅብረተሰቡ ጋር በተደረጉ ውይይቶች እንዲዳብሩ መደረጉን የተናገሩት የክልሉ ፕሬዚዳንት፤ የሕግ ማሻሻያዎቹ በምክር ቤት ቀርበው መጽደቃቸው የክልሉን ሕዝብ አሳታፊ ያደረገ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ አቶ ሙስጠፌ ገለጻ፤ በክልሉ የተደረጉ የሕግ ማዕቀፍ ማሻሻያ ሥራዎች ወደ መሬት ወርደው ተግባራዊ ሲሆኑ የተለያዩ የቢሮ አደረጃጀቶች በማስተካከል አሠራራቸውን የሚያዘምኑ ይሆናሉ።

በሕግ ማሻሻያው አማካኝነት የተቋማቱ አደረጃጀትና አሠራር ማስተካከያ ሲደረግ ደግሞ የመሠረተ ልማት ግንባታን በቅንጅት በመምራትና የኅብረተሰቡን ወቅታዊ ጥያቄዎች ለመመለስ ይረዳል ሲሉ ተናግረዋል።

የክልሉ ምክር ቤት አባላት የአርብቶና ከፊል አርብቶ አደሩን እንዲሁም በከተሞች ያለውን ኅብረተሰብ የሚጠቅሙ የተቋማት አደረጃጀትና ምቹ አሠራር ላይ ያተኮሩ የሕግ ማሻሻያዎች መደረጋቸውን አድንቀው፤ የክልሉ ተቋማቱ ይበልጥ ቅንጅት ባለው መልኩ መሥራት እንዳለባቸው አስተያየት ሰጥተዋል።

የምክር ቤቱ አፈጉባኤ ወይዘሮ አያን አብዲመሐመድ በበኩላቸው፤ በክልሉ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ያደረጉ ውይይቶች መደረጋቸውን ገልጸው፤ የክልሉ የሥራ አስፈጻሚ አሠራር ማስተካከያ አዋጅ ምክር ቤቱ ከሚወያይባቸው አጀንዳዎች መካከል አንዱ መሆኑን ጠቁመዋል።

የሶማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጉባኤ ዛሬ የሚጠናቀቅ ሲሆን በትናንትናው መድረክ የክልሉ የፋይናንስ አሠራር ማሻሻያ፣ የማዕድንና ኢነርጂ ማሻሻያ፣ የከተማና የገጠር የውሃና ፍሳሽ አሠራር ማሻሻያ አዋጆችን አጽድቋል።

# በስድስት ወራት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ባለፉት ስድስት ወራት ክትባት ከተሰጣቸው የእንስሳት በሽታዎች ዋናዎቹም የዶሮ ፈንግል በሽታ፣ ደስታ መሰል በሽታ፣ የአፍሪካ የፈረስ በሽታ፣ የግመል ፈንጣጣ እንዲሁም የከብቶችና የፍየሎች ሳንባ ምች መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

በዚህም መሠረት የዶሮ ፈንግል በሽታ ከ21 ሚሊዮን በላይ ዶዝ፣ የበግና ፍየል ፈንጣጣ 12 ሚሊዮን በላይ ዶዝ፣ የበግና ፍየል ደስታ መሰል በሽታ 11 ሚሊዮን በላይ ዶዝ፣ ከ25 ሚሊዮን በላይ ዶዝ ደግሞ የፍየሎች ሳንባ ምች፣ የከብቶች ሳንባ ምች፣ የአፍሪካ የፈረስ በሽታና የግመል ፈንጣጣ መሆናቸውም ተገልጿል፡፡

ድንበር ዘለል ለሆኑና ላልሆኑ የእንስሳት በሽታዎች ክትባት መሰጠቱንም የእንስሳቱን ጤና ከመጠበቅ ባሻገር ከሰው ወደ እንስሳት የሚተላለፉ በሽታዎችን መግታት መቻሉን በግብርና ሚኒስቴር የእንስሳት ጤናና ቬተርነሪ ፐብሊክ ሄልዝ መሪ ሥራ አስፈፃሚ ዶክተር ውብሸት ዘውዴ አመልክተዋል፡፡

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የፈጠራ ሥራዎች የሚበረታቱበት መርሀ ግብር

ወርቅነሽ ደምሰው

የዲጂታል ዘመኑን የዋጁ የዓለም ሀገራት በቴክኖሎጂ ዘርፍ የተራቀቀ ደረጃ ላይ ደርሰዋል። ይህም ከዘመኑ ጋር አብሮ ለመራመድ የዲጂታሉን ዓለም መቀላቀል አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባል። በዲጂታል አብዮት ወደ ኋላ የቀሩ ሀገራት በእዚህ ላይ በትኩረት መስራት ይጠበቅባቸዋል፤ እነዚህ ሀገሮች በዲጂታል ቴክኖሎጂው ወደፊት ከገሰገሱ የዓለም ሀገራት ጋር ለመወዳደር የሚያስችላቸውን ስትራቴጂ መቀየስም ይኖርባቸዋል።

ኢትዮጵያ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ የሚያስችላትን ዲጂታል ኢኮኖሚ በመከተል «ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ»ን አጽድቃ ወደ ሥራ ገብታለች። በሀገሪቱ ቀደም ሲል የዲጂታል ዘርፉ ትኩረት ያልተሰጠው በመሆኑ ብዙ አልተሰራበትም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ለዲጂታል ዘርፉ በተሰጠው ትኩረት የቴክኖሎጂ መሠረት ለመጣል የሚያስችሉ ተግባሮች እየተከናወኑ መሆናቸውን እንደ አበረታች ጀምር መውሰድ ይቻላል።

በቅርቡ ኢትዮ ቴሌኮም ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የሚያስችል «ኢትዮ ቴል ኢኖቬሽን» የተሰኘ ቴክኖሎጂን መሠረት ያደረጉ አዳዲስ ቢዝነሶችና ባለሙያዎች የሚበረታቱበት መርሐ ግብር ማስጀመሩም የዚሁ ጥረት አንዱ ማሳያ አድርጎ መውሰድም ይቻላል።

ፕሮግራሙን አስመልክተው የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ፍሬሕይወት ታምሩ እንዳሉት፤ ይህ ፕሮግራም ጀማሪ ቴክኖሎጂ መሠረት ያደረጉ ቢዝነሶችና ባለሙያዎች የሚበረታቱበት ሲሆን፤ በጀማሪ የሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ የሚሰማሩ ተቋማትን የሚያበረታታና የማኅበረሰቡን ችግር በመፍታት የራሱን ሚና ይጫወታል። ፕሮግራሙ ለ250 ጀማሪ ኩባንያዎች ዕድል ይሰጣል።

የአሸዋ ቴክኖሎጂ ሶሉሽን አክሲዮን ማህበር መስራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዳንኤል በቀለ በንግድ ስራ የተሰማሩ ናቸው። ከሚያካሂዱት የንግድ ስራ ጎን ለጎን ዘመናዊ ንግድን ማዘመን የሚችሉበትን መንገድ ከመወጠን ባለፈ ጥናቶችን አድርገዋል፤ ከዚያም አሸዋ ቴክኖሎጂ የሚል ኩባንያ በማቋቋም በኦንላይን ግብይት ውስጥ ገብተው እየሰሩ ይገኛሉ።

አቶ ዳንኤል በቀለ እንደሚሉት፤ «ኢትዮ ቴል ኢኖቬሽን» የተሰኘ ፕሮግራም መጀመሩ የኢንኩቤሽን ማዕከል መፍጠር ወይም የቢዝነስ ሀሳብ ያላቸው ሰዎች በስልጠና፣ በትምህርት እና በፋይናንስ በማበረታታት በዘርፉ ያላቸውን ብዙ ልምድ እንዲጠቀሙበት የሚያደርግ ነው። ይህም ወደ መሬት የሚወርድ ሥራ እንዲኖር የሚያደርግ በመሆኑ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው። የፈጠራ ባለሙያዎች ሀሳባቸው እውን እንዲሆንም ያግዛል። ለሀገርም ሆነ የፈጠራ ሀሳብ ላላቸው ባለራዕዮች ትልቅ እድል የሚሰጥና ከፍተኛ ፋይዳ ያለውም ነው።

‹‹ብዙ ሀሳብ እና ራዕይ ያላቸው በርካታ ወጣቶች አሉ›› ያሉት አቶ ዳንኤል፤ «የፈጠራ ሀሳቦችን በማበረታታት ሰዎች ከህልማቸው ጋር እንዲገናኙ ወይም ሃሳባቸው እንዲሳካላቸው በፋይናንስም ሆነ በስልጠና ድጋፍ በማድረግ ማገዝ ይገባል። » ሲሉ ይገልጻሉ። በሀገሪቱ የፈጠራ ሀሳቦች በማበረታታት ላይ ብዙ እንዳልተሰራም ተናግረው፣ ተደራሽነታቸው ሰፊ ባይሆንም እንደ «ብሉሙን» አይነት ጥቂት ተቋማት ኢንኩቬሽን ማዕከልን በመፍጠር የፈጠራ ሀሳቦችን በማበረታታት ረገድ እየሰሩበት እንደሚገኙም ነው የጠቀሱት።

«ከአሜሪካ እና ህንድ ጋር ሲነጻጸር በሀገራችን እየተካሄደ ያለው የዲጂታል ዘርፉ እንቅስቃሴ ደካማ ነው። ህንድን ብንመለከት በዲጂታል ዘርፉ ላይ የምታደርገው እንቅስቃሴ በቢሊዮን ዶላር የሚያስገኝላት ነው። » ያሉት አቶ ዳንኤል፣ የአሜሪካውን አፕልን የመሳሰሉ በአለም ላይ ትልቅ ተጽዕኖ ያመጡ ተቋማት ብዙ ትሪሊየን ዶላር በዚህ ቴክኖሎጂ እንደሚያፋሱም ይጠቅሳሉ። ቻይናም እንዲሁ 95 በመቶ የሚሆነው ህዝቧ ዲጂታል ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ መሆኑን ያብራራሉ።

ይህ የሚያመላክተው የየሀገራቱ መንግሥታት ለዘርፉ ትኩረት ሰጥተው በደንብ መሥራት መቻላቸውን ጠቅሰው፣ ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ መንግሥት ለዘርፉ ሲሰጥ የነበረው ትኩረት በጣም አናሳ መሆኑን ያመለክታሉ።

«እኛ እንደ ሀገር የምንነቃው ሌሎች የዓለም ሀገራት ጥለው ብዙ ርቀት ከተጓዙ በኋላ ነው። ለአብነት የግብርናውን ዘርፍ ብንመለከት በመንግሥት ትኩረት አግኝቶ እየተሰራ ያለው ገና አሁን ነው። ዓለም አሁን ያለችበት ሁኔታና እኛ ያለንበት ሁኔታ ሲነጻጸር ብዙ ወደኋላ የቀረንበት ሁኔታ ስለመኖሩ መገንዘብ እንችላለን» ይላሉ።

አቶ ዳንኤል እንደሚናገሩት፣ በኢትዮጵያ የዲጂታል ዘርፉ አዲስና እንግዳ ከመሆኑ አንጻር ወደ ዘርፉ ሊሰማራ ያሰበ ሥራ ፈጣሪ፣ ንግድ ፈቃድ ከማውጣት ጀምሮ እስከ ግብር መክፈል ድረስ ብዙ ወጣ ውረድ ያለው ሂደት ለማለፍ ሊገደድ ይችላል። በአንጻሩ ደግሞ የሀገሪቱ ህዝብ ጊዜውን የሚያውለውም ሆነ ገንዘቡን ወጪ የሚያደርገው የውጪ ሀገር ሶፍት ዌር ወይም ቴክኖሎጂ በመጠቀም ላይ ነው። በሀገር ውስጥ በልጽገው የሀገርን ችግር የሚፈቱና የኢትዮጵያን ህዝብ የሚያገለግሉ ምርቶች ለገበያ እንዲወጡ ለማድረግ መንግሥት በትኩረት መሥራት አለበት።

«ለአብነት በዲጂታል ዘርፍ የሚሰማሩ ሥራ ፈጣሪዎች ለተወሰኑ ዓመታት ከታክስ ውጪ ቢደረጉ ይበረታታሉ፤ ጎልተው የሚታዩበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። የፖሊሲ እገዛ ቢደረግ፤ ይበልጥ የሚሳለጥበት ሁኔታ በመፍጠር የተሻለ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል» የሚሉት አቶ ዳንኤል፤ «አሁን እየወጡ ባሉ ፖሊሲዎች እኛንም በማሳተፍ ለፖሊሲ ግብዓት የሆኑ መረጃዎችን በመውሰድ ጸድቆ ሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሁኔታ መኖሩ የሚያበረታታና ትልቅ ለውጥ ያመጣል» ብለዋል።

ቴክኖሎጂ የሕዝብን ሕይወት ቀላልና ምቹ፣ ዘመናዊና የተሻለ እንዲሆን እንደሚረዳ ጠቁመው፣ ስርአተ ትምህርት ተቀርጾለት በትምህርት መሰጠት አለበት ብለው እንደሚያምኑም ያመለክታሉ። ወደ ዘርፉ የሚገባ ሰው ልምዱን ሲያወቀውና ጥቅሙን ሲረዳ ነው የተሻለ ለውጥ ማምጣት የሚችለው ያሉት አቶ ዳንኤል፣ ይህ ሲሆን ባለሀብቱም ጉዳዩን በትኩረት መመልከት እንደሚችል ነው ያብራሩት።

አቶ ዳንኤል እንዳሉት፤ ብዙ ኩባንያዎች የተቋቋሙት በኢንኩቤሽን ማዕከል ነው። አንድ ሀሳብ ያለው አንድ ሥራ ፈጣሪ ህልም ይዞ ይመጣል። ይህ ህልም በደንብ ይገመገማል፤ችግር ካለበት እዚያው ጋ ብዙ ሳይለፋበት ገንዘብ፣ ጊዜ እና ጉልበት ሳይወጣበት ይቀራል። ቀጣይነት ያለውና ዘላቂ ከሆነ ደግሞ በደንብ መውጣት ይችላል። በዚህ ሂደት የጠሩ ሀሳቦችና ቢዝነሶች የተሻለ ተፅጽኖ በመፍጠር ለማህበረሰቡ የሚደርሱበት እድል ይፈጠራል።

እነዚህ ሥራዎች አንደኛ እንደ ቢዝነስ ብዙ ገንዘብ የሚያመጡ ሲሆን፤ ሁለተኛ ደግሞ እንደ ሀገር ከሥራ ፈጠራ አንጻር የተሻለ እድል በመፍጠር ሰፊ የሥራ እድል እንዲኖር ያደርጋሉ። በአጠቃላይ በዲጂታል ዘርፍ ላይ ያሉ ችግሮችን በመፍታት የተሻለ ለውጥ ለማምጣት ያስችላሉ።

«ሁሉም ነገር የጀመረው ከሀሳብ ነው፤ ዓለምን የቀየራት ፈጠራ /ኢኖቬሽን/ ነው። አለም አሁን ያለችበት ደረጃ ላይ ለመድረሷ መነሻው ሀሳብ ነው። ስለዚህ ሀሳብ በደንብ መደገፍና መደነቅም አለበት» ይላሉ። ምክንያቱም ለአዳዲስ ነገሮች ትኩረት አልሰጠንም ማለት በድሮ በሬ በማረስ የመቀጠል ህልም ይዘን የምንጓዝበት ሁኔታ መኖሩን ነው የሚያሳየው። አዲስ ሀሳብ እንደሀገር ኢኮኖሚ የሚቀይርልንና የተሻለ ተፅጽኖ እንድንፈጥር የሚረዳን በመሆኑ መንግሥት የተጀመሩ ሥራዎችን ቶሎ ሥራ ላይ ማዋል አለበት» ሲሉም ያብራራሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ግንዛቤ ላይ ብዙ ክፍተት ያለ በመሆኑ በደንብ ቢሰራ ለውጥ ማምጣት ይቻላል። በሀገሪቱ ከ30 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች ኢንተርኔት ይጠቀማሉ። በዚህ እየተጠቀሙ ያሉት ውጪ ያሉ ኩባንያዎች ናቸው። በሀገር ውስጥ የበለጸጉት ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ መንግሥትና ሥራ ፈጣሪው በጋራ የሚሰሩበት የተሻለ የሚያሻግር ነገር መፍጠር የሚችልበት ሁኔታ ሰፊ ነው። ሀገር የሚገነባው በጋራ ነውና የመንግሥትና የግሉ ዘርፍ ግንኙነት በጣም ጠንካራ መሆን አለበት።

«እኔ ወደ ዘርፉ ስቀላቀል ያጠራቀምኩትን ብር ይዤ ነው የተነሳሁት። ወደ አክሲዮን ሽያጭ የገባሁት ለማስፋፊያ ነው» የሚሉት አቶ ዳንኤል፤ እንደ ሥራ ፈጣሪ ወደ ሥራ ሲገቡ ወደ ብዙ ችግሮች እንዳጋጠሟቸውም ያስታውሳሉ። ሥራ ፈጣሪዎች እንደዚህ አይነት ኢንኩቤሽን ማዕከል ላይ ተቀላቀለው የገንዘብ ሆነ የእውቀት ድጋፍ አድርገው ህልምና ዓላማ ተጋርተው ሀሳባቸው ወደ ሕዝቡ እንዲመጣ እገዛ ማግኘታቸው ቀላል ነገር አይደለም። ብዙ ሽክም በመቀነስ የተሻለ ደረጃ የሚደርሱበት ሁኔታ የሚፈጥርና ከውጭ ሀገራት ጋርም የልምድ ልውውጥ ስለሚኖር የተሻለ እድል እንዳለው ይገልጻሉ።

አቶ መርዕድ በቀለ የአይ ኢ ኔትዎርክ መሥራችና ዋና ሥራ አስፈጻሚ ናቸው። በቴክኖሎጂው ዘርፍ ተሰማርተው ወደ ሥራ ከገቡ 14 ዓመታትን አስቆጥረዋል። ለተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ላልሆኑ ተቋማት ትላልቅ የዳታ ማዕከላትን ከመገንባት ጀምሮ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅትን ያቋቋሙ ሲሆን አገልግሎቱን የሚሰጡትም አገር በቀል በሆኑ ባለሙያዎች ነው። አቶ መርዕድ የፈጠራ ባለሙያዎችን ማበረታታት ለኛ ሀገር አዲስ ነው ይላሉ።

በሌላው ዓለም በተለይ በፋይናንስ የሚረዳና እንዴት መሥራት እንዳለባቸው የሚያግዙ ብዙ አሠራሮች እንዳሉም ይናገራሉ። «የፈጠራ ሀሳብ ይዘው ለሚመጡ ባለሙያዎች ገንዘብ ይሰጣቸዋል። ያንን ሀሳብ እንዴት አድርገው ወደ መሬት በማወረድ ውጤት እንደሚያመጡ ደግሞ የማኔጅመንት፣ የማርኬቲንግ፣ አሠራሮችን የሚመለከቱ የሙያ ድጋፍ ይደረግላቸዋል ሲሉ ገልጸው፣ ይሄ በብዙ ሚሊዮን ዶላር የሚንቀሳቀስ ራሱን የቻለ ኢንዱስትሪ መሆኑን ይገልጻሉ።

አሁን ላይ ኢትዮ ቴሌኮም ይህንን ፕሮግራም መጀመሩ በጣም የሚበረታታ መሆኑን ጠቅሰው፣ የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶለት ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ እንደሚገባም አቶ መርዕድ ይጠቁማሉ። አንድ ፈጠራ ውጤት እስከሚያመጣ ድረስ ረጅም ጊዜ ሊወስድ እንደሚችልም አስገንዝበው፣ ልክ እንደ ኢትዮቴሌኮም ሌሎች ድርጅቶችም የፈጠራ ሀሳቦችን ማገዝ ቢችሉ ጥሩ ነው ይላሉ። ብዙ ሀሳብ ያላቸው፣ ብዙ ችግር መፍታት የሚችሉ ሰዎች ሀሳባቸው ከግብ ሳይደርስ ተወስነው የሚቀመጡበት ሁኔታ መኖሩን ጠቅሰው፤ እነዚህን አካላት በማገዝ ለሀገር ከፍተኛ ሚና መወጣት ይገባል ብለዋል።

ዘመኑ የዲጂታል መሆኑን በመጥቀስ፣ ብዙ ፈጠራዎች ከዲጂታል ቴክኖሎጂ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን አቶ መርዕድ ይናገራሉ፤ ብዙ አገልግሎቶችን ወደ ዲጂታል ለመቀየር፣ ፍጥነትና ቅልጥፍናቸውን ለማሻሻል የሚሰሩ የሶፍትዌር፣ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስና የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን የሚያበለፅጉ ወጣቶችን መርዳት በዲጂታል ኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግም ይናገራሉ።

አቶ መርዕድ እንደሚሉት፤ የፈጠራ ሰዎች ገንዘብ ለማግኘት ባንክ መሄድ የለባቸውም። በግሉ ሴክተር ያሉ ሰዎች የፈጠራ ባለሙያዎችን መርዳትና ማገዝ የሚችሉበትን ሁኔታ መፍጠር አለባቸው። የፈጠራው ውጤት መሬት ላይ ወርዶ ውጤት ሲያመጣ ደግሞ ከትርፉ ይካፈላሉ። አሁን ባለው ሁኔታ በሀገራችን አንድና ሁለት የውጭ ኩባንያዎች አሉ እንጂ ዘርፉ ይህንን ሥራ የሚሰሩ ድርጅቶችን በመፍጠር ረገድ ብዙ ስራ ይቀረዋል። የፈጠራ ባለሙያዎች በታገዙ ቁጥር ብዙ ችግሮች ይፈታሉ። በገንዘብም፣ በፖሊሲም፣ በሕግም እና በሌሎች ማበረታቻዎች ሊታገዙ ይገባል። በሌላ በኩል የፈጠራ ባለሙያዎች የታክስ ማበረታቻ እንዲያገኙ ማገዝ እንዲሁም ብድር የሚያገኙበትን ሁኔታም ማመቻቸት ያስፈልጋል።

«እኔ ወደዚህ ሙያ ስገባ በራሴ ጥረት ከማድረግ በዘለለ በፋይናንስም ሆነ በማኔጅመንት ምንም የሚያግዝ አሠራር አልነበረም» ያሉት አቶ መርዕድ፤ አሁን የተሻሉ ጅምሮች እንዳሉም ይገልጻሉ። በዚህ ዘመን በፈጠራ ሥራ ላይ የሚሰማሩ ሰዎች የተሻለ እድል እንዳላቸውም ገልጸው፣ «ሀገራችን በእድገት ወደኋላ ቀርታለች፤ በፍጥነት መሻገር የምንችለው በዲጂታል ቴክኖሎጂ በመሆኑ የፈጠራ ስራ የሚሰሩ ባለሙያዎችን ማበረታታት ይገባል» ይላሉ።

ዲጂታል ኢኮኖሚ በትምህርት፣ በጤና፣ በትራንስፖርት፣ በአገልግሎትና በሌሎች መስኮች በሀገር እድገት ላይ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ጠቁመው፤ «መንግሥትና የፋይናንስ ኢንዱስትሪው ላይ አተኩሮ ዘርፉ የሚያድግበትን ዘዴ በመቀየስ ትኩረት ተሰጥቶ ቢሰራ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሀገራችን ማደግ በምትፈልገው ፍጥነት ማድግ ትችላለች» ብለዋል።

> **አሁን ላይ ኢትዮ ቴሌኮም ይህንን ፕሮግራም መጀመሩ በጣም ያበረታታል፤ ይህ አይነቱ መርሀ ግብር የአሠራር ሥርዓት ተዘርግቶለት ቀጣይነት እንዲኖረው ማድረግ ይገባል። አንድ ፈጠራ ውጤት እስከሚያመጣ ድረስ ረጅም ጊዜ ሊወስድ ይችላል፤ ልክ እንደ ኢትዮ ቴሌኮም ሁሉ ሌሎች ድርጅቶችም የፈጠራ ሀሳቦችን ማገዝ ቢችሉ ጥሩ ነው**

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ ትንታኔ

# የተዳከመው የቱሪዝም ዘርፍ

ክብረአብ በላቸው



ኢትዮጵያ የብዙ ባሕላዊ እና መንፈሳዊ እሴቶች እንዲሁም የተፈጥሮ እና ሰው ሠራሽ ቅርሶች ባለቤት መሆኗ የሚታወቅ ሐቅ ነው። ብዙ የሚዳሰሱ እና የማይዳሰሱ የሀገሪቱ ቅርሶች መኖራቸውም የሚታወቅ ሲሆን፣ እነዚህም በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የባሕል እና የሳይንስ ተቋም (ዩኔስኮ) ተመዝግበው ይገኛሉ። ይህም በዓለም መድረክ ሀገሪቱን ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው ተመራጭ ሊያደርጋት እንደሚችል አያጠያይቅም። ነገር ግን ኢትዮጵያ በዘርፉ የምታገኘው ገቢ ልታገኝ ትችል ከነበረው እጅግ ጥቂቱን መሆኑን የተለያዩ የዘርፉ ባለሙያዎች ሲናገሩ ቆይተዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ጭራሽ ዘርፉ በተለያዩ ምክንያቶች ዝቅተኛ አፈፃፀም እያሳየ መምጣቱ እየተዘገበ ይገኛል። ይህንኑ ዝቅተኛ አፈፃፀም በቅርቡ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፕላን እና ልማት ሚኒስቴር ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባቀረበው ሪፖርቱ ይፋ አድርጎል። ይህ ለምን ሆነ? ስንል ያነጋገርናቸው የኢኮኖሚ እና የቱሪዝም ዘርፍ ባለሙያዎች የሚሉት አላቸው።

የምጣኔ ሃብት ባለሙያው አቶ ወሰንሰገድ አሰፋ እንደሚናገሩት፤ ዋና ዋና የኢኮኖሚ ዘርፎች ከሚባሉት ከግብርና እና ኢንዱስትሪ ቀጥሎ የሚመጣው የአገልግሎት ዘርፍ ውስጥ የቱሪዝም ዘርፍ ዋነኛው ነው። ሦስቱ በሀገር ኢኮኖሚ ውስጥ ዋናውን ድርሻ እንዲይዙ የሚፈለግ ሲሆን፤ አገልግሎት ደግሞ በዋናነት ቱሪዝምን ያካትታል። ከአገልግሎት ዘርፍ በላይ እንዲመራ የሚፈለገው የኢንዱስትሪ ዘርፍ ነው።

ነገር ግን የተረጋጋ ኢኮኖሚ እንዲኖር ደግሞ የአገልግሎት ዘርፉ በተለይም ቱሪዝም ማደግ እንዳለበት አያጠያይቅም ይላሉ። በኢትዮጵያ ውስጥ ከጠቅላላ ምርት ትልቁን ድርሻ የያዘው የአገልግሎት ዘርፉ ነው የሚሉት ባለሙያው ቀጥሎ ግብርና፣ በሦስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው ደግሞ ኢንዱስትሪ ሲሉ ያስረዳሉ። በእርግጥም አገልግሎት ውስጥ ካሉት ከዋንኞቹ አንዱ ቱሪዝም ነው። ይህ ዘርፍ ራሱን የቻለ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ኖሮት የሚመራ ነው ሲሉ የምጣኔ ሃብት ባለሙያው አቶ ወሰንሰገድ ይናገራሉ።

ቱሪዝምን የሀገር ውስጥ እና የውጭ በሚል በሁለት መክፈል ይቻላል የሚሉት የምጣኔ ሃብት ባለሙያው፤ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኘው ከውጭ የሚመጣው ቱሪዝም ነው ይላሉ። አሁን የቱሪዝም ዘርፉ ለምን ወደቀ? ከተባለ ቱሪዝም በዋንኛነት የሚያድገው ምንም እንኳ ሊጎበኝ የሚችል ሰፊ ሃብት ቢኖርም የሀገር ውስጥ ደህንነት እና መረጋጋት ካልተረጋገጠ ዘርፉ ስኬት ማስመዝገብ አይችልም ሲሉ ይገልጻሉ። ስለዚህ መረጋጋት በሀገሪቱ ውስጥ የማይኖር ከሆነ በምንም ዓይነት ተዓምር ከቱሪዝም የሚገኘው ገንዘብ ከፍ ሊል እንደማይችል በመጠቆም፤ ሰላም ከቱሪዝም የማይለይ መሆኑን ያስረዳሉ።

ሌላው በዓለም አቀፍ ደረጃ የቱሪስቶች ወይም የሰው የመጎብኘት ፍላጎት የሚኖረው የዓለም ኢኮኖሚ በራሱ የተረጋጋ ሲሆን ነው። የሚሉት አቶ ወሰንሰገድ የእርስ በእርስ ጦርነቶች እያሉ እና ሀገራት ከሀገራት ጋር እየተጋጩ ከሆነ የኢኮኖሚ ቀውስ ስለሚኖር ቱሪዝም የሚጎዳበት ሁኔታ እንደሚፈጠር ያብራራሉ። በተለምዶ ለመዝናናት ጉዞ የሚያደርጉ ሰዎች ያላቸው የመክፈል አቅም የተዳከመ እየሆነ ከመጣ እና የውጭ የተለያዩ ምክንያቶች እንደ ኮቪድ ያሉ እና ሌሎች ተላላፊ በሽታዎች ከፍ እያሉ በሚመጡበት ጊዜ ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር የሚመጡ የቱሪስቶች ቁጥሩ በሚታይ መልኩ መቀነሱ የሚያስገርም አለመሆኑን ያስረዳሉ ።

አቶ ወሰንሰገድ እንደሚናገሩት፤ቱሪዝም ላይ ምንም ያህል የሚጎበኝ ሰዎችን ሁሉ ሊስብ የሚችል ሥራ ቢሠራም የሚጎበኛው ሰው ከሌላ ሄዶ ሄዶ ገቢ አይኖረውም። ፣ ስለዚህ ቱሪስት ወደ ሀገር ውስጥ እንደይመጣ ከላይ የተጠቀሱ ዓለም አቀፍ ምክንያቶች እንዳሉ ሆነው ዋናው ግን ዓለም አቀፍ ከሆኑ ጉዳዮች በላይ በሀገር ውስጥ ያለው ሰላም እና መረጋጋት ወሳኝ ነው።

ባለፉት ዓመታት በሀገሪቱ የተስተዋሉ ግጭቶች እና ጦርነቶች ለዘርፉ ማዳከም የነበራቸው ሚና ከፍተኛ ነው። ጎብኚው ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል እንዲሁም በአጠቃላይ ወደ ተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በሚንቀሳቀስበት ወቅት እና ጊዜ ጥቃት ይደርስብኛል ብሎ የሚያስብ ከሆነ ተንቀሳቅሶ የመጎብኘት ፍላጎት አይኖርም። ስለዚህ ክልሎችም ከዘርፉ የሚገኘው ገቢ እንዲጨምርላቸው ከፈለጉ በክልላቸው ውስጥ ሰላምን ማስከበር መቻል እንዳለባቸውም ተናግረዋል።

የሰላም መረጋገጥ ለቱሪዝም ዘርፍ ለነገ የማይባል ሥራ ነው የሚሉት የምጣኔ ሃብት ባለሙያው፤ ከዚህ ውጪ ቱሪስቶች ሲመጡ የሚጠቀሟቸው ሆቴሎች፣ የሎጀስቲክ አገልግሎት፣ የመኪና አቅርቦት፣ የአየር ትራንስፖርት እንዲሁም በቱር እና ትራቭል ወይም በአስጎብኚነት ሥራ የተሰማሩ ድርጅቶች የሚሰጡዋቸው አገልግሎቶችን ማዘመን ያስፈልጋል ብለዋል። እንዲሁም የውጭ ምንዛሪ በቀላሉ እና ቶሎ ቶሎ የሚቀያይሩ ባንኮች መኖራቸውም የቱሪስት ፍሰቱ እንዲጨምር ያደርጋል ብለዋል።

አቶ ወሰንሰገድ በማብራሪያቸው፣በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙ ችግሮችን ለመቅረፍ የግሉ ዘርፍ እና መንግሥት ተናበው መሥራት እንደሚጠበቅባቸው በመግለፅ በዋናነት ግን የሀገሪቱን ሰላም እና ደህንነት ማስጠበቅ የመንግሥት ዋነኛው የቤት ሥራ እንደሆነ አንስተዋል።

የቱሪዝም ባለሙያው ዶክተር አያሌው ሲሳይ በበኩላቸው፤ ለኢንዱስትሪው መዳከም የተለያዩ ምክንያቶች እንደነበሩ ያብራራሉ። በዓለም አቀፍ ደረጃ በወረርሽኝ መልኩ የተከሰቱ በሽታዎች እንዲሁም በሀገሪቱ ውስጥ የነበረው ጦርነት ዘርፉን በእጅጉ ጎድቶታል ካሉ በኋላ፤ ተዘግቶ እንዲቆይም አድርጎታል ይላሉ። በተጨማሪነት ቱሪዝም እና ሰላም አብረው የሚሄዱ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች በመሆናቸው፤ ሰላምም ወሳኝ እንደሆነ በመግለፅ፤ ከምጣኔ ሃብት ባለሙያው ጋር ተመሳሳይ ሃሳብ እንዳላቸው ያስረዳሉ።

የቱሪዝም ባለሙያው ዶክተር አያሌው፤ ሀገሪቱ የሚጎበኝ ሃብት አላት፤ መስሕብ አላት፤ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ቱሪስት ለመሳብ ዝግጁ የሆኑ እና ቱሪስቱም የሚወዳቸው መስሕቦች አሉ። ሀገሪቱንም ሆነ ሕዝቡን ቱሪስቶች ይወዱዋቸዋል። ነገር ግን በተለይ በውጭ ቱሪስቶች ሃብቶቹ እንዳይጎበኙ ዓለም አቀፍ እና ሀገራዊ ችግሮች ምክንያት ሆኖዋል። ነገር ግን ከላይ የተጠቀሱት ነገሮች የሚወዱትን መስሕብ፣ የሚወዱትን ሕዝብ፣ የሚወዱትን ቅርሶች እንዳይጎበኙ አድርጓቸዋል። ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ዓለም አቀፍ ቱሪዝም ተዘግቷል ይላሉ።

ከዛ ውጭ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዓለም የቱሪዝም ድርጅት ለቱሪስቶች እንዴት ብለው ሀገራትን መጎብኘት እንዳለባቸው፤ ከጤናቸው አኳያ የተለያዩ መመሪያዎችን ስለሰጧቸው፤ የዓለም አቀፍ ቱሪስቶቹ ስለሁሉም ነገር ያውቃሉ። በሀገር ደረጃ ደግሞ ምንም እንኳ ኮቪዱ እየተቃለለ ቢመጣም አሁንም ለጥንቃቄ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማድረግ የግድ ነው። በሌላ በኩል የተጠናከረ ዲፕሎማሲ እንዲሁም ቅስቀሳ ያስፈልጋል፤ ሰላም ተፈጥሯል፤ ሀገሪቱን መጎብኘት ትችላላችሁ መባል አለበት። ራሱን ችሎ የተቋቋመ የቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድን ጨምሮ የክልል የቱሪዝም ቢሮዎች እጅ ለእጅ ተያይዘው ቱሪስቶች ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጡ ጥረት ማድረግ እና ማስታወቂያዎችን መሥራት አለባቸው ይላሉ።

‹‹ይህ ማለት አሁን ዝም ብለው ተቀምጠዋል ማለት አይደለም›› የሚሉት የቱሪዝም ባለሙያው ዶክተር አያሌው፤ አዲስ ስትራቴጂ ነድፈው ዘርፉ እንዲያንሰራራ ለማድረግ የሚቻልበትን መንገድ ሁሉ ቀይሰው ወደ ዓለም የቱሪዝም ገበያ መሄድ እና አጠናክረው መሥራት አለባቸው ለማለት ነው። ከድሮው በበለጠ ሥራዬ ብለው በኢትዮጵያ ሰላም እንደተፈጠረ ማስተዋወቅ አለባቸው ብለዋል።

‹‹ዛሬ ብትመጡ ምንም ዓይነት ችግር አይገጥማችሁም። ›› የሚለውን በሙሉ በገበያው ላይ በተጠናከረ መልኩ መሥራት አለባቸው ሲባል፤ የቱሪዝም ቤተሰብ የሚባሉት ሌሎችም ሆቴሎች ፣ አስጎብኚ ድርጅቶች ወዘተ ሁሉ ግንባር ፈጥረው ወደ ዓለም ቱሪዝም ገበያ መዝመት እና በተዓማኒነት ቱሪስቱን የመቀስቀስ ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል ይላሉ።

ሰላምን ማረጋጋጥ ከተቻለ የኮቪዱ ሁኔታ እየተቃለለ ከሄደ፣ ሀገሪቱን ቱሪስቶች የሚወዷት በመሆኑ ይመጣሉ የሚል ተስፋ እንዳላቸውም ይገልፃሉ። ዶክተር አያሌው በተጨማሪ ሲናገሩ፤ በየአካባቢው ከዚህም ከዛም ትንኮሳ ወይም ሀገሪቱ ሰለላሟን እንዳታገኝ የሚደረጉ ጥረቶችን ለማስተካከል መንግሥት ኃላፊነቱን ከተወጣ እና ሕዝቡም ተገቢውን ሚና ከተጫወተ ቱሪዝም የዚህች ሀገር ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት መሆን እንደሚችልም ተናግረዋል።

አሁን ላይ ለቱሪዝም ምቹ የሆኑ ግብዓቶች እየተገኙ ለዓለም አቀፍ ቱሪስት የሚሆኑ ለአብነት በክልሎች ጎርጎራ፣ ወንጪ፣ኮይሻ እንዲሁም አዲስ አበባ ውስጥም የወዳጅነት አደባባይ፣ አንድነት ፓርክ፣ እንጦጦ ፓርክ እነኚህ ሁሉ ተጨማሪ ለቱሪስቱ የተዘጋጁ ስለሆኑ እነኚህንም ጨምሮ የነበሩትንም አጠናክሮ ማሠራት ከተቻለ ለወደፊቱ ኢትዮጵያ የቱሪስቶች መናኸሪያ ትሆናለች ብለው እንደሚያምኑም አብራርተዋል።

የወደፊቱን በተመለከተም የሚናገሩት አቶ ወሰንሰገድ፤ በዋናነት መንግሥት ሰላምን ከማስጠበቅ አንፃር ትክክለኛ ሥራ የማይሠራ ከሆነ የቱሪዝም ዘርፉ ብቻ ሳይሆን፤ ማንኛውም የኢኮኖሚ ዘርፍ በትክክል ውጤታማ መሆን እንደማይችልም ተናግረዋል። ስለዚህ መንግሥት ይህን ችግር ለመቅረፍ የሚያስችል ስትራቴጂ ነድፎ ሁሉም ነገር ወደ ተረጋጋ ሁኔታ መቀየር እንዲችል መሥራት እንዳለበትም ነው የተናገሩት።

በተጨማሪም የቱሪዝም ሚኒስቴር ትልቅ የቤት ሥራ ይጠብቀዋል ያሉት የቱሪዝም ባለሙያው አቶ ወሰንሰገድ አሰፋ፤ የቱሪዝም አይነቶች በጣም ብዙ ስለሆኑ ኢትዮጵያውያንም የራሳቸውን ሀገር የመጎብኘት ልምምድ ሊኖራቸው እንደሚገባ አንስተዋል። በተለይ የመንግሥትም ሆነ የግል ድርጅት ሠራተኞች በዓመት አንድ ጊዜ የጉብኝት ፕሮግራም እንዲኖራቸው በማድረግ የተለያዩ የሀገሪቱን ክፍሎች እንዲጎበኙ ማበረታታት እንደሚገባ ያነሳሉ። ይህም የሀገር ውስጥ ቱሪዝሙን ለማነቃቃት ፋይዳው የጎላ እንደሚሆንም በምሳሌነት አንስተዋል።

ባለሙያዎቹ እንደገለፁት፤ በቀጣይ በተለይም መንግሥት የሀገሪቱን ሰላም እና ደህንነት ከማስጠበቅ አንፃር ኃላፊነቱን በሚገባ ከተወጣ እና ሰላም መስፈኑን በተመለከተ በሰፊው የማስተዋወቅ ሥራ ከተሠራ የቱሪዝም ሃብት ሰፊ በመሆኑ ትልቅ ውጤት መምጣቱም የማይቀር መሆኑን ተናግረዋል።

ማህበራዊ

# ሴቶች

# አከራካሪው የሕግ ታራሚ ሴቶች ልጅ የመውለድ መብት

**ሰላማዊት ውቤ**

የሕግ ታራሚ አስናቀች ጌታቸው ቃሊቲ የሴቶች ማረሚያና ማረፊያ ቤት በ2006 ዓ.ም ነው የገባችው። የ20 ዓመት የነፍስ ግድያ ፍርደኛ በመሆኗ አሁንም የቅጣት ጊዜዋን እየፈፀመች ትገኛለች። እሷ ጥፋተኛ በተባለችበት የነፍስ ወንጀል ተከሳሾች ሰባት ነበሩ። ቅጣቱ የተጣለባቸው በዛው በተከሰሱበት 2006 ዓ.ም በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት እንደሆነም ታወሳለች። በወቅቱ ሰባራ ባቡር ተብሎ በሚጠራውና አሁን አራዳ በተባለው እሷ በቀረበችበት ፍርድ ቤት ከታሰረችበት አዲስ አበባ ፖሊስ 23 ጊዜ ተመላልሳ ውሳኔ አገኘች። ውሳኔ ያገኘችው በሦስት ዓመት ከሰባት ወሯ መሆኑንም ታነሳለች።

«እንደ ወንጀል ሕግ ሦስት መሠረታዊ ነገሮች ሲከናወኑ አንድ ሰው ጥፋተኛ ሊሆን ይችላል» የምትለው ታራሚዋ ከሦስቱ አንዱ እሷ እንደነበረችና ለሟቹ ምክንያት እኔ ነኝ ብላ ቃሏን በመስጠቷ እንደተፈረደባትም አጫውታናለች። እሷ እንደምትለው ከሟች ቤተሰቦች ጋር በኦሮሞ ገዳ ሥርዓት በአገር ሽማግሌ እርቅ ፈፅማ የፍርድ ሂደቷን በመከታተል ላይ ትገኛለች።

ከዚህ ቀደም በማረሚያ ቤቱ የሞት ፍርደኛ ከብዙ መብቶች ይገለል ነበር። ትምህርትም አይማርም ነበር። በአሁኑ ሰዓት ግን የሞት ፍርደኛ በዕድሜ ልክ ተፈቅዶለት ከመሠረተ ትምህርት ጀምሮ እስከ ፈለገው ድረስ የሚማርበት ዕድል ተመቻችቶለታል። እሷም ብረታ ብረትና ኮምፒውተርን ጨምሮ በተለያዩ ሙያዎች በመሰልጠን ትሠራለች። ምርቶቿን በመሸጥም ተጠቃሚ ሆናለች።

ታራሚዋ እንደነገረችን በሙያዋ ፖሊስ የነበረች በመሆኗ ማረሚያ ቤት ከመግባቷ በፊት የነበረውን አብዛኛውን ጊዜዋን በስልጠና ነው ያሳለፈችው። በመሆኑም ነገ ዛሬ እያለች ትዳር ቶሎ አልያዘችም። እንዲህም ሆኖ በ2006 ዓ.ም ወደ ማረሚያ ቤቱ ልትገባ አካባቢ ትዳር መሥርታና የራሷን ጎጆ ቀልሳ ነበር። ነገር ግን ልጅ አልወለደችም። ልጅ ሳትወልድ ዘንድሮ በማረሚያ ቤት ውስጥ ሆና 38ኛ ዓመቷን ይዛለች። የመውለጃ ጊዜዋ ሊያከትም ጥቂት ዓመታት ብቻ ቀርተዋታል። ሆኖም መውለድ ሰብዓዊ መብት ነው በመሆኑም የግድ መውለድ አለብኝ የሚል አቋም አላት።

ታራሚው ባትወልድም በማረሚያ ቤት ቆይታዋ በማረሚያ ቤቱ ያሉ ሴት ታራሚዎችን ልጆች እንደ ልጆቿ ተንከባክባ አሳድጋለች። በማረሚያ ቤቱ ካሉት ሴት ታራሚዎች ቀደም ብላ ወደ ማረፊያው መግባቷ ሕፃናት ልጆቻቸውን እንድትንከባከብላቸው አስችሏታል። አስናቀች የታራሚ ሴት ኮሚቴ አባልም ነች። በኮሚቴው በኩል ከማረሚያ ቤቱ ጋር በመሆን ከማረሚያ ቤት መልካም ትምህርት አያገኙም በሚል ልጆቻቸው ወደ ሕፃናት ማሳደጊያ እንዲሄዱ ትሠራለች። አንዲት የምትወዳትና እንደ ልጇ ተንከባክባ ያሳደገቻት ሕፃን ሰላም የተሰኘ የሕፃናት መንደር እንድትሄድ በማድረጉ ሚና አላት። ይህችን ልጅ እንደ ልጇ ታያትና ትቆጥራት ስለነበር ስትነጠላት አብዝታ እንዳለቀሰችም ታራሚዎችና የማረሚያ ቤቱ ኃላፊዎች ይመሰክሩላታል።

ሆኖም ማረሚያ ቤት ለሕፃን መልካም ሥፍራ ባለመሆኑ ልጅቱ ከዛ በመራቋ ደስተኛ ነበረች። ግን ደጋግማ እንደምትለው ልጅ መውለድ የሰብዓዊ መብት በመሆኑ ሴት እስረኞች የመውለድ መብታቸው ሊከበርላቸው ይገባል ስትል ትጠይቃለች።

በዚህ በቃሊቲ የሴቶች ማረሚያና ማረፊያ ቤት እንደ አስናቀች ልጅ ያልወለዱ ሌሎች ታራሚዎችም አሉ። የመውለጃ ዕድሜያቸው በእስር ሊያልፍባቸው መሆኑ አብዝቶ እንደሚያሳስባቸው ሲናገሩ ይደመጣሉ። የመውለጃ ጊዜያቸው በዛው በእስር ቤት ያለፈባቸው ታራሚዎችም ይገኛሉ። እነዚህም የመውለጃ ጊዜያቸው በማለፉ አብዝተው የሚቆጩበት ሁኔታ አለ።

በተለያየ ደረጃ ያሉ የማረሚያ ቤቱ ኃላፊዎች ይሄንን ያውቁላቸዋል። በተለይ ሴቶቹ ሕግ ማስከበሩ እንደ ተጠበቀ ሆኖ እንደ ወላድ ሴት የመውለድ ሰብዓዊ መብት ስሜታቸውን ይጋሩላቸዋል።

«ስሜታቸው ይሰማኛል»ይላሉም በፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የሴቶች ማረሚያና ማረፊያ ማዕከል ኃላፊ የሆኑት ምክትል ኮሚሽነር ዓለም ጥላሁን፤ምክትል ኮሚሽነሯ በተለይ የሕግ ታራሚ አስናቀች አብዝታ ልጅ ስለመውደዷና መውለድ ስለመፈለጓ እንደሚያውቁ



‹‹የመውለጃ ሰብዓዊ መብቴ በእስር ሲያልፍብኝ ነው››የሕግ ታራሚ አስናቀች ጌታቸው



ምክትል ኮሚሽነር ዓለም ጥላሁን



ፎቶ ገባቦ ገብሬ

የሕግ ባለሙያ ተሾመ እሸቱ

ይናገራሉ። እንደ አስናቀች ሁሉ ሌሎችም ታራሚዎች የመውለጃ ዕድሜያቸው ሳያልፍ በብርቱ መውለድ መፈለጋቸውን ይጠቅሳሉ። ይሄ የታራሚዎቹ ፍላጎትና ሁኔታ እንደማንኛውም ሰብዓዊ ፍጡር በተለይም እንደ ሴትና ኃላፊም የሚሰማቸው መሆኑን ይገልጻሉ፤በተለያዩ መድረኮች የታራሚዎቹን ሀሳብ በማንሳት የሚያንፀባርቁ መሆናቸውንም ይናገራሉ። የመውለጃ ጊዜያቸው በእስር ምክንያት የሚያልፉቸውና ዘር የመተካት ዕድል ያጡ ታራሚ ሴቶች የመውለጃ ጊዜያቸው ሳያልፍ የሚወልዱበት ሁኔታ ቢመቻች እንደሚፈልጉም ያወሳሉ ምክትል ኮሚሽነር ዓለም።

ሰው ወንጀል የሚሠራው በማወቅም ባለማወቅም፤ በቸልተኝነትም እንደሆነ ደጋግመው የሚያወሱት ምክትል ኮሚሽነሯ የሰው ልጅ አንዳንድ ጊዜ ለሰኮንድ መታገስ እያቃተው ትልቅ ወንጀል ውስጥ በመግባት ብዙ መብቶቹን የሚያጣበት ወይም ሊያሳካቸው በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ የሚገባበት ጊዜ እንዳለም ይጠቅሳሉ። ይሄን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ቢያንስ ሴት ታራሚዎች የሚወልዱበት ሁኔታ ቢመቻች መልካም መሆኑንም ያብራራሉ። «ፈጣሪ ከፈቀደለት የሰው ልጅ ዘር ተክቶ ቢያልፍ መልካም ነው»ሲሉም ያክላሉ።

ይሁንና ይሄ የሴት ታራሚዎች በእስር ምክንያት መውለጃ ዕድሜ ማለፍ ጉዳይ እንደ ማረሚያ ቤት እስከ አሁን ከመድረክ ግብዓትነት ባለፈ የተሠራበት አለመሆኑንም ይናገራሉ። በጉዳዩ ላይ ከሰብዓዊ መብት አንፃር መሠራት አለበት የሚልም እምነት አላቸው ምክትል ኮሚሽነሯ ።

ይሄ የሕግ ታራሚ ሴቶች መብት በሕግ ዓይን እንዴት እንደሚታይ የሕግ ባለሙያም ጠይቀን ነበር። በኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለ21 ዓመታት ያገለገሉት የሕግ ባለሙያው አቶ ተሾመ እሸቱ የሴት ታራሚዎቹ የመውለድ መብት የሰብዓዊ መብት ጉዳይ እንደሆነ በማስቀደም ምላሻቸውን ሰጥተውናል።

ቢሆንም ከወንጀል ሕግ አንፃር እንዲህ በዋዛ ምላሽ የሚያገኝ አለመሆኑን ያነሳሉ። እንደ ባለሙያው ማብራሪያ ታዲያ ሕጎቹ ሲወጡ ተልኳቸው ምንድነው? ምን ያክል የኅብረተሰቡን ችግር ይፈታሉ? የሚለው ይታያል። የወንጀል ሕግ በባሕርይው ዋና ዓላማው ሰዎችን ማስተማር ሲሆን ሁለተኛው ዓላማው የተረጋጋ ኅብረተሰብ እንዲኖር ማድረግ ነው፤ ለምን ቢባል አንድ ወንጀል ሲፈፀም ወንጀሉ በተፈጸመበት አካባቢ ያለ ኅብረተሰብ ይረበሻልና ነው። ይሄ ማለት የተለያዩ እንቅስቃሴዎቹ ይስተጓጎላሉ፤ የተለያዩ ማኅበራዊ መስተጋብሮቹም ይደነቃቀፋሉ። በንብረት ላይ የተለያየ ጉዳት ይደርሳል። ሰዎች ሊፈናቀሉ ይችላሉ። ሕጉ ታዲያ ይሄን ተጎጂ ኅብረተሰብ ከጉዳት ይከላከላል። በሌላ በኩል ሕጉ ጎጂው አካል በፈፀመው ጥፋት እንዲማር የማድረግ ዓላማ ይኖረዋል። የመብት ጉዳይም ቢሆን ሴቲቱ ወንጀል ስትፈጽም ገና በዕዳ አሲዛዋለችና ከምግብና መጠጥ እንዲሁም መጠለያ ውጪ መነሳቱ በፍፁም አይታሰብም። የመውለድም መብት ቢሆን በዚህ ረገድ እንደሰብዓዊ ጥያቄ ይቅረብ እንጂ

## አንዱ ኢትዮጵያ ውስጥ ታራሚ ሴቶች እንዳይወልዱ የሚደነግግ ሕግ የለም። እንዲሁም ወንጀል ሰርተው ቢታሰሩም ይውለዱ የሚል ሕግ የለም

ተቀባይነቱ አጠራጣሪ ነው።

ሰዎች ለምን ይታሰራሉ ለምንስ ከባድ ቅጣት ይወሰንባቸዋል በተለይ ሴቶች ለምን ለረጅም ጊዜ ይታሰራሉ ? የወንጀል ሕግ መሠረቱ ኅብረተሰብን የመጠበቅ ጉዳይ ከሆነ ኅብረተሰብን ያወኩ ሰዎች ለረጅም ጊዜ መታሰራቸው የማይቀር ይሆናል። ኅብረተሰቡ በድርጊቱ ታምሷል አልታመሰም ? የሚለውም የሚታይ ነው። በድርጊቱ አባት አልባ የሆነ ልጅ አለ የለም? ባሏን ያጣችስ ሴት አለች የለችም? ጧሪ ያጣ ወላጅስ አለ የለም? የሚለው ይፈተሻል። በተለይ በገጠሩ ባሏ የሞተባት ሴት ድጋሚ የማግባት ዕድሏ የመነመነ ነው። ምክንያቱም ሁለት ሦስት ልጅ ይኖራታል። ልጆቿን ይዞ የሚያገባ ወንድ የለም። ሦስት አራት ልጅ መውለድ ስትችል ባሏ ሞቶባታል። በመሆኑም አንድ እንደወለደች ልትቀር ትችላለች። ውጤቱ በጣም ከባድ የሚያደርገው ይሄ ነው። እነዚህ ሰዎች ሊማሩ፤ማኅበራዊ ግንኙነታቸው ጤናማ ሊሆን፤አዕምሯቸው የተረጋጋ ሊሆን ይችላል ወይ ተብሎ ሲታሰብ አንዳንዶቹ ሰው ሊጠሉ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ደም ለመመለስ የሚሹ ይሆናሉ። በመሆኑም ጉዳቱ እስር ቤት የገቡ ብቻ ሳይሆን እስር ቤት ያልገቡትም ጭምር ነው። ፍርዱ የሚሰጠውም ይሄን ጉዳት በማመዛዘን ነው።

እንደ ባለሙያው ታዲያ ሴቶች ለረጅም ጊዜ ማረሚያ ቤት ይቆያሉ። የመውለጃ ጊዜያቸው ያልፋል። መውለድ ተፈጥሯዊና ሰብዓዊ መብት ነው የሚለው አያከራክርም። ይሄ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ሁለት ጭብጥም ያነሳሉ። አንዱ ኢትዮጵያ ውስጥ ታራሚ ሴቶች እንዳይወልዱ የሚደነግግ ሕግ የለም። በተመሳሳይም ሁለተኛው ወንጀል ሠርተው ቢታሰሩም አይውለዱ የሚል ሕግ የለም የሚለው ነው። እንዲወልዱ የሚፈቅደውን ሕግ ጥሶም እንዳትወልድ የፈረደ ዳኛም የለም ባይ ናቸው። እንደ ማብራሪያቸው ታዲያ ሆኖም ሳይወልዱ የመቅረት አደጋ የተጋረጠባቸው ሴቶች ማረሚያ ቤቶች ውስጥ አሉ። ሆኖም ይውለዱ ተብሎ እስካሁን የተሰጠ ውሳኔም የለም። እንዲወልዱ የሚለውን ሕግ ጥሶ የተሰጠ ውሳኔም የለም። ቢሆንም መውለድ ሰብዓዊ መብት ነውና በቅንነት ተነሳስተን እንየው ቢባል እንኳን መውለድ ሰብዓዊ መብቷ መሆኑን የምታነሳው ሴት በሕይወት የመኖር መብት ያለውን ሰው በራሷ ውሳኔ ገድላዋለች። የሰብዓዊ መብት ጥያቄ እያነሳ ያለው ማነው ፤ምን ያደረገ ሰው ነው? ሲባል በሕይወት የመኖር መብትን የገሰሰ ሰው ነው። በዚህ ምክንያትም እንድትታረም ማረሚያ ቤት የገባች ሴት ናት ጥያቄውን እያነሳችው ያለችው፤ ጥያቄውን እንቀበለው ቢባልም ሕጎች ኅብረተሰብ የሚጠብቁና አድሏዊ መሆን የለባቸውም። በተጨማሪም ሕጎች ተፈፃሚም መሆንም አለባቸው።

አድሏዊ መሆን የለባቸውም የሚለውን ሲያብራሩት ትዳሩ የተበተነና ልጆቹ አላሳዳጊ የቀሩበት ወንድ አለ። ሰው ከመግደሉ በፊት 30 ዓመት ከገደለ በኋላ 25 ዓመት ቢፈረድበት 55 ዓመት ይሆነዋል። ከዚህ በኋላ ትዳር ይዞ ቢወልድ የልጁን ፀጋ ውጤት ሊጠቀምበት ይችላል ወይ? ሲባል ማንም ሰው መውለድ የሚፈልገው የሚያሳድገው ልጅ ነው። የሚያስተምረው፤ ጤንነቱን የሚንከባከብለት፤የተሟላ አዕምሮ እና ጤንነት ያለውን ልጅ ነው መውለድ የሚፈልገው። የማኅበረሰቡን ሀብት ተጠቅሞ አድጎ ለማኅበረሰቡ አስተዋፅዖ የሚያደርግ ሰው ነው መውለድ ያለበት። 50 ዓመት ከሞላኝ የወለድኩት ልጅ እኔም ለእሱ አልሆንም እሱም ለእኔም ለኅብረተሰቡም አይሆንም። ጎዳና ላይ ወጥቶ ይበጠብጣል።

በሌላ በኩል በሴትና በወንድ ታራሚ መካከል አድሎ የሚፈጥር ሕግ ልናወጣ እንችላለን ወይ የሚለው ያነጋግራል። እንዲህ ዓይነት ሕግ ቢወጣ ማረሚያ ቤት ውስጥ ሊተገበር ይችላል ወይ? ቤት ያሉ ሴቶች ጽንስ የማስወረድ ጥያቄ እያነሱ ባሉበት እውነት ልጅ ናፍቀው ነው ወይ ጥያቄውን ያነሱት የሚል እሳቤ በሚነሳበት ወቅት የታራሚዎቹ የመውለድ ጥያቄን ምን ያክል በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ይኖረዋል የሚለውንም መመልከቱ አስፈላጊ ነው። የማይፈፀም ሕግ መውጣት የለበትምና ሕጉ ከወጣ እንዴት ሊፈጸም እንደሚገባ ከወዲሁ መጠናት አለበት። የማይፈፀም ሕግ መውጣት የለበትም። እንዴት ነው፤የት ነው የሚፈፀመው፤መቼ ነው የሚፈፀመው፤ማነው የሚያስፈፅመው ማረሚያ ቤቱ ነው፤ማኅበራዊ ጉዳይ ነው፤ ፍርድ ቤት ነው ሲሉ ይጠይቃሉ ባለሙያው። ይወለድ ቢባል የት ይኖራል? ትዳር ያልነበራቸው እንዴት ነው የሚወልዱት ባል አግብተው ነው ወይስ ለመውለድ ሲባል ከሆነ ሰው ጋር ተገናኝተው ነው? በዚህ ላይ በዝርዝር መነጋገርም ይጠይቃል። አፈፃፀሙ ከባድ ነው። የከበደ ሁሉ ሊሆን አይችልም ማለት አይደለም። የወንጀል ሕግ ዓላማ ማኅበረሰብን ማረጋጋት ነው የሚለውን ዓላማ እንዳይጎዳ መጠንቀቅም ይገባል። ወንጀል ፈጻሚን ይሄን ያህል መብት ካለኝ ወንጀል መፈፀም የተባረከ ነው ሊያሰኝም ሁሉ ይችላል።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

**ኃይለማርያም ወንድሙ**

በ1985 ዓ.ም በጥርና በየካቲት ወራት እንዲሁም በ1956 በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ለንባብ የበቁ ዘገባዎችን ዛሬ ለትውስታ ያህል መራርጠን እንመለከታለን፡፡ ሮይተርስን ምንጭ በማድረግ የተሰራ አንድ አስገራሚ ዘገባ «በንቦች የተነደፈ ሰው ሞተ ይለናል፡፡ ምን አድርጎ? እንዴት ሞተ? የሚለውን ዝርዝር እንድታነቡት እንጋብዛለን፡፡ ሠፋሪዎች የእርሻ በሬ አገኙ፡፡ ነጋዴዎቹ ሱቅ አገኙ፡፡ በገለብ ሐመር አካባቢ ፖሊሶች ፀጥታ ከማስጠበቅ አልፈው ለነዋሪዎቹ እርሻ እያስተማሩ አስደሳች ጥቅም አስገኝተዋል የሚሉን ሌሎች ዘገባዎችንም እንደሚከተለው ለንባብ ጋብዘናል፡፡

**አንድ ሺህ ጊዜ የተነደፈው ሞተ**

ዛፎችን በመከርከም ላይ እንዳለ ከአንድ ሺህ ጊዜ በላይ በንቦች የተነደፈው የአውስትራሊያ ማዘጋጃ ቤት አንድ ሠራተኛ ሞተ፡፡

ዳረን ፐሪየር የተባለው የ25 ዓመት ሰው ባለፈው ሳምንት ረቡዕ ዕለት አንድ የንብ ቀፎ በቀሰቀሰበት ወቅት በአንድ ተንጠልጣይ ወለል ( መሰላል) ላይ ሆኖ ዛፎችን በመከርከም ላይ ነበር፡፡ የንቦቹ ጥቃት ለማስቀረት ሲሉ ሰውዬውን ወደ መዋኛ ገንዳ ውስጥ ወርውረው ሲከቱት የዐይን ምሥክሮች እንዳሉት ከሆነ ግለሰቡ ሙሉ በሙሉ በንቦች ተሸፍኖ ነበር፡፡

ሮይተርስ ( የካቲት 7 ቀን 1985 ከታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

**ሠፋሪዎች የእርሻ በሬዎች አገኙ**

ጎባ፤ (ኢ-ዜ-አ) በባሌ ዞን በሐረዋ ዘጠኝ በጃሚ ሠፈራ መንደር ለሚገኙ ሦስት መቶ ስልሳ ሁለት አባወራ ሠፋሪ ገበሬዎች የእርሻ በሬዎች ባለፈው እሁድ ታደላቸው፡፡

የእርሻበሬዎችእደላያስፈለገውበሐረዋከነበሩት ዘጠኝ የሠፈራ መንደሮች መካከል የስምንቱ መንደር ገበሬዎች ደርግ በተደመሰሰበት ወቅት በተፈጠረው አለመረጋጋት ያላቸውን ንብረትና ቤት ሸጠው ወደ ትውልድ ሥፍራቸው ሲሔዱ የጃሚ ሠፈራ መንደር ሠፋሪዎች ግን መንደራቸውን ለቀው ባለመሔድ መንደራቸውን ከዘራፊዎችና ከወንበዴዎች ተከላክለው ለመቆየት በመቻላቸውና በወቅቱ በነበረው አለመረጋጋት ምክንያት የደረሰባቸውን ችግር ለማቃለል እንዲቻል ነው፡፡

ሦስት መቶ ስልሳ ሁለት በሬዎችን በ ፪፻፲፫ ሺህ ብር ገዝቶ ለሠፋሪ ገበሬዎች በነፍስ ወከፍ ያደለው የእርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን (እማማኮ) ነው፡፡ በዕደላው ወቅት ለእያንዳንዱ ገበሬ በትክክል መድረሱን የሚያረጋግጥ ደረሰኝ ከሠፈራ መንደሩ ሊቀመንበር ከአቶ ታደለ አስፋው የተረከቡት አቶ ተስፋዬ ለታ የባሌ ዞን እማማኮ ተወካይ ናቸው፡፡

አቶ ኃይለማርያም ሁንዴ የባሌ ዞን እርዳታ ማስተባበሪያና ማቋቋሚያ ኮሚሽን የግብርና ቴክኖሎጂ ኃላፊ ማብራሪያ ከዋናው መሥሪያ ቤት አንድ ቡድን ሠፈራው ድረስ ሔዶ ችግራቸውን ካጠና በኋላ የእርሻ በሬዎች መግዛታቸውን ጠቅሰው፤በሬዎቹ ከዞኑ እማማኮ ፤ከግብርና ከገበሬው የተውጣጡ አባላት ያሉት ኮሚቴ ተቋቁሞ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በክልሉ ባሉ የወረዳ ገበሬዎች በመዘዋወር ተገዝተው ለማከፋፈል መቻሉን ገልጠዋል፡፡ (ጥር 1ቀን 1985 ከታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

**ነጋዴዎች ሱቅ አገኙ**

አዲስ አበባ ፤(ኢ-ዜ-አ) በመርካቶ አካባቢ ጆንያ ተራ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በ፲፫፻፶፪ ሱቅ ለተቃጠለባቸው ግለሰቦች መንግሥት ከአንድ ሚሊዮን ተኩል በላይ ያሠራው ሱቅ የክልል ፲፬ ምክር ቤት ባፈው ማክሰኞ በእጣ አከፋፈለ፡፡ ሱቅ የተቃጠለባቸው ግለሰቦች ከአምስት ዓመት በላይ ቦታ ሳይሰጣቸው የቆዩ ከመሆኑም በላይ ለእነሱ ተብሎ የተሠራው ሱቅ ከዓመት በፊት የተጠናቀቀ ቢሆንም በተለያዩ ምክንያቾች በመጓተቱ መንግሥት የሚያገኘው ገቢ እንደቀረና ሰዎቹ እንደ ተጉላሉ ተገልጧል፡፡

የሱቆቹ ክፍፍል የተደረገው የክልል ፲፬ የኢኮኖሚ አገልግሎት ዘርፍ የባለሱቆችን አቤቱታ ትኩረት በመሥጠት ከባለጉዳዮች ጋራ ከሰባት ጊዜ በላይ በመሰብሰብ የተቃጠለባቸውን ሰዎች በማጣራት ለዘጠና ነጋዴዎች ደርሰዋል፡፡ ነጋዴዎቹ በሰጡት አስተያየት ራሳቸው ያቋቋሚቸው ኮሚቴዎችም ሆኑ ያለፈው አስተዳደር በተለያዩ ምክንያቶች ጉዳዩን ሲያጓትቱት ቢቆዩም የክልል ፲፬ አስተዳደር ፍትሐዊ በሆነ አሠራር ችግራቸውን መፍታቱ ያስደሰታቸው መሆኑን ገልጠዋል፡፡ (ጥር 10 ቀን 19 85 ከታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ)

**የፖሊሶች እርሻ**

በገለብና ሐመር ባኮ አውራጃ የሚገኙ ፖሊሶች ከፀጥታ ጥበቃቸው ጋር ሕዝቡን ስለ እርሻ ጥቅም ያስተምራሉ፡፡ ከዚህ ቀደም ባሳዩት የእርሻ አዝመራ አስደሳች የጤፍ ምርት አግኝተዋል፡፡ ባለፈው ዓመትም እርሻቸውን በጥራጥሬ ዘር ሞክረውታል ፡፡ መሬቱም ፍጹም ድንግል በመሆኑ ፤አስደሳች የሆነውን ምርት አግኝተዋል፡፡

ሕዝቡም የፖሊሶቹን አርአያ በመከተል የእርሻን ሥራ እንደሚያስፋፋና የራሱን ኑሮ እንደሚያሻሽል ፖሊሶች ተስፋ ያደርጋሉ ፡፡ (መስከረም 6 ቀን 1956 ዓ.ም ከታተመው አዲስ ዘመን ጋዜጣ )

# ዓለም አቀፍ

## አሜሪካ ዜጎቿ በአፋጣኝ ሩሲያን ለቀው እንዲወጡ አዘዘች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

በአሜሪካና በሩሲያ መካከል የተፈጠረው አለመግባባት ሰንበትበት ቢልም በዩክሬን ጉዳይ ሁለቱ አገራት በያዙት ተጻራሪ አቋም ልዩነታቸው እየሰፋ መጥተዋል፡፡ በዩክሬን ባለው ጦርነት፣ በሩሲያ የህግ አስከባሪ ተቋማት እየተደረገ ነው በተባለ የዘፈቀደ እስራትና ወከባ አሜሪካ ዜጎቿ ሩሲያን ለቀው እንዲወጡ ተናግራለች፡፡

በሞስኮ የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ "በሩሲያ ውስጥ የሚኖሩ ወይም ወደ ሀገሪቱ የሚጓዙ አሜሪካዊያን ወዲያውኑ ሩሲያን መልቀቅ አለባቸው" የተባለ ሲሆን ኤምባሲው "ህጋዊ ያልሆነ የእስር አደጋ ስላለ ጥንቃቄ እንዳይለያችሁ" ሲልም አክሏል፡፡ አሜሪካ ዜጎቿ ሩሲያን ለቀው እንዲወጡ ደጋግማ ስታስጠነቅቅ ቆይታለች፡፡

እንደዚህ ያለ የመጨረሻ የህዝብ ማስጠንቀቂያ ያወጣችው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ጦራቸውን በከፊል ለማንቀሳቀስ ካዘዙ በኋላ በመስከረም ነበር ተብሏል፡፡

"የሩሲያ የደህንነት አገልግሎት የአሜሪካ ዜጎችን 'በውሸት' ክስ በቁጥጥር ስር አውሏል፡፡ ሩሲያ ውስጥ የሚገኙ የአሜሪካ ዜጎችን ለእስር እና ለእንግልት እየዳረገ ነው፡፡ ፍትሃዊና ግልጽ የሆነ አያያዝ ከልክለዋል፡፡ በሚስጥር ችሎት ወይም ተአማኒነት የሌለው ማስረጃ ወይም ማስረጃ ሳያቀርቡ ጥፋተኛ እያሉ ነው" ሲል ኤምባሲው ገልጿል፡፡

ሩሲያ በስለላ ጠረጠርኩት ያለችውን የአሜሪካ ዜጋ የወንጀል ክስ እንደከፈተች የፌዴራል ደህንነት አገልግሎት (ኤፍኤስቢ) በጥር ወር ማስታወቁን ሮይተርስ ዘግቧል፡፡






## የናይጄሪያ ጦር በአገሪቱ ምርጫ ወቅት መፈንቅለ መንግሥት ማቀዱ ተጠቆመ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የናይጀሪያ ገዢ ፓርቲ የአገሪቱ ጦር ምርጫ ወቅት መፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ እያሴረ ነው ማለቱን ቢቢሲ ዘግቧል፡፡

ኤፒሲ የተሰኘው የገዢው ፓርቲ አመራር የሆኑት ፖለቲከኛው የጦር ጄነራሎች ባለፈው ሳምንት ከኤፒሲ ተቀናቃኝ ከሆነው ፒዲፒ ፓርቲ ፕሬዚዳንታዊ ዕጩ ጋር ሚስጥራዊ ስብሰባ ያደረጉ ሲሆን፤ የናይጀሪያ ጦር ግን መጪውን ምርጫ ለማስተጓጎል መፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ አሲሯል መባሉን አስተባብሏል፡፡

ጦሩ ይህንን ውንጀላ "በክፋት" እና "በተንኮል የተሞላ" ነው ሲል ባወጣው መግለጫ ማጣጣሉ የተነገረ ሲሆን በአፍሪካ ከፍተኛውን የሕዝብ ቁጥር በያዘችው ናይጀሪያ የቀጣዩን ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ አሸናፊን መገመት እጅጉን አዳጋች ሆኗል፡፡

የካቲት 17/2015 ዓ.ም. በሚካሄደው ምርጫ ቦላ ቲንውቡ ከገዢው 'ኦል ፕሮግረሲቭ ኮንግረስ' (ኤፒሲ)፤ አቲኩ አቡበከር ከ'ፒፕለስ ዴሞክራቲክ ፓርቲ' እና ፒተር ኦቢ ከሰራተኞች ፓርቲ ፕሬዚዳንት ለመሆን ጠንካራ ፉክክር የሚያደርጉ ዕጩዎች ናቸው፡፡

ታዲያ 'ኦል ፕሮግረሲቭ ኮንግረስ' ፓርቲን ወክለው ለፕሬዚዳንትነት የሚወዳደሩት ቦላ ቲንውቡ የናጀሪያ ጦር መፈንቀለ መንግሥት ለማድረግ እያሰሬ ነው ማለታቸውን ተከትሎ ሠራዊቱ ባወጣው መግለጫ ጦሩ "ለሕገ መንግስቱ ታመኝ ነው" በማለት አስተባብሏል፡፡ ሠራዊቱ ጨምሮም የሲቪል አስተዳደርን ለመፈንቀል በሚሸረብ ሴራ ውስጥ ፈጽሞ ሊሳተፍ አይችልም ብሏል፡፡

"የናይጀሪያ ጦር ኃይል በብዙ ፈተና የተገኘውን ዴሞክራሲ ለመቀልበስ የሚደረግ ሴራ አካል ፈጽሞ ሊሆን አይችለም" ሲሉ የጦሩ ቃል አቀባይ ብርጋዴር ጄነራል ቱከር ጉሳው ተናግረዋል፡፡ መንግሥትና ዋና ዋና የፖለቲካ ፓርቲዎች ሰራዊቱ በሰጠው መግለጫ ላይ አስተያየት አልሰጡም፡፡ የደኅንነት ስጋት፣ የነዳጅ እጥረትና የአዳዲስ ገንዘብ ኖቶች እጥረት ላሳሰባቸው ናይጀሪያዊያን የአገሪቱ ጦር መፈንቅለ መንግሥት እያሴረ ነው መባሉ እምብዛም ግድ አልሰጣቸውም፡፡

# ነፃ ሃሳብ

# ለዛሬ ችግሮቻችን ከትናንት ታሪኮቻችን እንማር

**ዳግም ከበደ**

አንድ ማኅበረሰብ በብዙ ፈተናዎች እና ውጣ ውረዶች ያልፋል። በድቅድቅ ጨለማ ተከቦ መውጫ የሚያጣበት፤ ዙሪያ ገባው ገደል የሚሆንበት ጊዜያት ብዙ ናቸው። የፈተናዎች መብዛት ጨለማውን የማይሻገረው፣ ተራራውን የማያልፈው መስሎ እንዲታይ ቢያደርገውም ከጨለማው በኋላ ብርሃን፣ ከገደሉ ውጪ ሰፊ ሜዳ መኖሩ ማሰብ ተገቢ ነው።

የቀደሙት አባቶቻችን "የማይገል ፈተና ያጠነክራል" ይላሉ። የማኅበረሰብን መንፈስ የሚረብሹ፣ ሕልውና የሚፈታተኑ፣ ትዕግስትን የሚገዳደሩ ጉዳዮች ይገጥሙናል። ጭራሹኑ የማያጠፉን እክሎች ለጊዜው ግን የጭቃ ውስጥ እሾክ ሆነው አላራምድ ይሉናል። ያን ጊዜ ነው ከቀደሙት አያቶቻችን ፈተናዎችና ብልሃቶች ለመማር የምንገደደው ።

ከመናወጥ ወዲያ መስከን፣ ከወጀቡ በኋላ ሰጥ ያለና የተረጋጋ ውቅያኖስ፣ ከፍፁም ተስፋ ማጣት ወደ ተረጋጋ ስብዕናና ስኬት እንደምንደርስ ከዛሬ ሳይሆን ትናንት ህያው ከነበሩ አባቶቻችን ታሪክ ለመማር የመነቃቃታችን እውነታ ችግሮቹን አሸንፈን ለመሻገር ትልቅ አቅም ይፈጥርልናል።

ለዚህ ደግሞ "ለመሆኑ ከዚህ ቀደም የት ነበርን? ዛሬስ የቱ ጋር ነው ያለነው?" ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት አሁን ሳይሆን ከሺህ ዘመናት ወዲህ በብዙ መልኩ ተፈትነዋል። አያት ቅድመ አያቶቻችን ይገቡበት ስፍራ ይሸሹበት ጥግ አጥተው ቀኑ ጨለማ የሆነባቸው ጊዜያትን ዞር ብለን ብንመለከት በብዙ መልኩ ትምህርት ልንወስድ እንችላለን።

እንዲያውም ዛሬ ሰቅዘው ለያዙንና እንፈታቸው ዘንድ ብልሃት ላጣንላቸው ስብራቶቻችን መፍትሔ እንደምናገኝ አያጠራጥርም። "በሽታውን ያወቀ መድኃኒት አያጣም" እንዲሉ ሕመሞቻችን ምን እንደሆኑ ዞር ስንል አቧራ የለበሱ የታሪክ ዶሴዎቻችን ይነግሩን ይሆናል። እኛ ግን ከትናንት ታሪኮቻችን ለመማር እንደ ማኅበረሰብ ምን ያህል ዝግጁ ነን?

ኢትዮጵያውያን ከሦስት ሺህ ዓመት ዘለግ ያለ የሀገረ መንግሥት ምሥረታ ታሪክ የነበረን እና በቀደምት ሥልጣኔ የዓለም ቁንጮ ባለታሪኮች ነን። ይህ አኩሪ ማንነታችን ግን መንገራገጭ የሌለበት አልጋ በአልጋ አልነበረም። ብዙ ወደ ኋላ መሄድ ሳይጠበቅብን ከ1760 እስከ 1847 ዓም ያለውን ታሪካችንን ብናገላብጥ ንጉሠ ነገሥታቸውን ንቀው፣ ጡንቻቸውን አፈርጥመውና "በማን ያህለኛል" ልባቸውን አሳብጠው በነበሩ መሳፍንቶች ኢትዮጵያውያን የሚጨነቁበት ዘመን እንደነበር መጥቀስ ይቻላል።

ዜጎች ይመሩበት ሥርዓት፤ይገብሩበት አስተዳደር አጥተው ልባቸው፣ ሃሳባቸው፣ መንፈሳቸውና አንድነታቸው እንደ አምባሻ ከብዙ ቦታ ተቆራርሶ ወደ ፈጣሪያቸው አንጋጠው ጥሩ ቀን እንዲመጣ የሚለምኑበት ግዜ ነበር።

"ኢትዮጵያዊነት ብዙ ሺህ ዘመናትን የተሻገረ ነው" የምንለው ምንም ችግር ሳይገጥመው እንደ ጅረት ኩልል ብሎ ፈስሶ ሳይሆን አለት ከሆኑ ችግሮች ጋር ተላትሞ፣ ጥልቅ ወደሆኑ ፈተናዎች ቁልቁል እንደ ፏፏቴ ውሃ ተፈጥፍጦ ከሰከነው ውቅያኖስ ጋር እንደሚቀላቀል ውሃ ባሕሪን ተላብሶ እንደሆነ ስለምንረዳ ጭምር ነው።

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ዛሬ ብቻ ሳይሆን ጥንትም በአያሌ መንገራገጭና መጣረዞች ውስጥ አልፏል። ኢትዮጵያውያን በአስተዳዳሪያቸው ብቻ ሳይሆን በማኅበራዊ መሪዎቻቸው፣ በተፈጥሮ፣ በውጪ ወራሪ በልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ተፅዕኖዎች ተፈትነዋል። ያ ሁሉ ግን ዛሬ ታሪክ ሆኖ ትውልድ የራሱን ውጣ ውረዶች እንዲመዝንበትና ትምህርት እንዲቀስምበት በዶሴዎች ላይ ተከትቦ ይገኛል።

ግዜው በ1888 ነው። ዓድዋ ላይ ውቅያኖስ አቋርጦ ሐቃችንን ሊበላና በግዞቱ ስር ሊያደርገን ያሰፈሰፈ የፋሺስት ጣሊያንን ጦር ሉዓላዊነታችንን ደፍሮ ድንበራችንን ጥሶ እደጃፋችን ጦር ሰብቆ የወረረን ወቅት። ኢትዮጵያዊነትና ኢትዮጵያውያን ከባድ የሕልውና ፈተና የተጋረጠብን ጊዜ። ይህ ጥቁር ቀን ግን አብዝቶ ይፈትነን እንጂ አንድነታችንን ገዝግዞ አልጣለውም። በእሳት ውስጥ ተፈትኖ እንደሚወጣ ወርቅ ክርናችንን አፈርጥሞ ድልንና ማሸነፍን፣ ኅብረትና አንድነትን፣ መተባበርና ፍቅርን አስተምሮን አለፈ። ፋሺስት ጣሊያን የሽንፈት ካባ ተከናንቦ የኢትዮጵያን ምድር ለቆ ወጣ።

ይሄ በውጪ ጠላት የተቃጣብን የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ጥቃት አልነበረም። አያሌ ጊዜያት መሰል ሕልውናችንን የፈተኑ፣ገንድሰው ሊጥሉን ከጫፍ ደርሰው ብዙ ሙከራዎች ነበሩ። እንደ ሕዝብ በጋራ የደማንባቸው፣ በአንድነት የቆሰልንባቸው፣ አልፎ ቀና ያልን ቢሆንም አንገታችንን የደፋንባቸው እዚህም እዚያም የነበሩ የታሪክ ክፍሎች ነበሩን።

ለበቀል ያሰፈሰፈው ጣሊያን ከ35 ዓመታት በኋላ ዳግም ኢትዮጵያን በመውረር ብዙ አትዮጵያውያንን በግፍ ለሞት የዳረገበት የጥቁር መዝገባችን ለዚህ ማሳያ ሊሆን ይችላል። የዓለም መንግሥታት ማኅበር (League of Nations) የተመሠረተ ቢሆንም ኢትዮጵያ ለዚሁ ማኅበር የዳግም የበቀል ወረራው በተመለከተ አቤት ብትልም አጋርነት ካሳዩ ጥቂት ሀገራት ውጭ ሰሚ ያጣችበትና በዓለም ሀገራት የተከዳንበት የጥቁር የኃዘንና የመከራ ታሪክ ክፍል አለን።

ኢትዮጵያውያን አንድ ሆንን። ደጋግሞ ዳር ድንበራችንን ሊፈትን የመጣን ጠብ አጫሪ አደብ ለማስገዛት አበርን። አርበኞች ሀገርን ላለማስደፈር ከፍተኛ ተጋድሎ አደረጉ። ቀዳማዊ አጼ ኃይለ ሥላሴ የጣሊያንን ድርጊት ለማስወገዝና በሕዝባቸው ላይ የተደቀነውን ፈተና ለማስቀረት ቢሞክሩም ሰሚ ሳያገኙ ቀርተው ለስደት ተዳረጉ።

በዚህ አስከፊ ግዜ ግን አውራውን እንዳጣ የቀፎ ንብ ሳይሆን እራሱንና ማንነቱን ጠንቅቆ የሚያውቅ፣ መሠረቱንና የተገነባበትን ፅኑ አለት የሚገነዘብ ኢትዮጵያዊ በዱር በገደሉ እራሱን ሰውቶ ፋሽስትን ዳግም አሳፍሮ ወደመጣበት መለሰው። ይሄ የሚያሳየን ኢትዮጵያዊነት በፈተናዎች ውስጥ ቢያልፍም የማይበገር መሆኑን ነው።

ማኅበረሰባችንን ሰቅዘው የያዙ ፈተናዎች መቼም ቢሆን የሚያበቁ አይደሉም። በየዘመናቱ እረፍት እየወሰዱ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን ይገዳደራሉ። የተፈጥሮ ድርቅ የማኅበረሰቡን ሌማት ባዶ አድርጎት ያውቃል። ገበሬም የሚዘራው ይቅርና የሚቀምሰው አጥቶ ነበር። ወረርሽኝ መልሶ መላልሶ ጎብኝቶናል።

የኅዳር በሽታ ተብሎ የሚታወቀው የአንደኛውን የዓለም ጦርነት ፍጻሜ ተከትሎ የተከሰተውና በመላው ዓለም ለ200 ሚሊዮን ሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው የእስፓኒሽ ፍሉ ወረርሽኝ የዚህ ማሳያ ሊሆን ይችላል።

መርስኤ ኃዘን ወልደ ቂርቆስ "የ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ" በተሰኘ የታሪክ መጽሐፋቸው ላይ እንደከተቡት በ1911 ዓ.ም የበሽታ መቅሰፍት በኢትዮጵያ ላይ ወርዶ ነበር። በዚያ ምክንያት ብዙ ሰው ማለቁን በታሪክ ከታባቸው ላይ አጫውተውናል።

መለስ ብለን ከተመለከትን የተፈተንባቸው እልፍ ጉዳዮች አሉ። የማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ምጣኔ ሃብታዊ ስንክሳሮች ከግራም ከቀኝም ጎነታትለውናል። ልንወድቅ ጫፍ ደርሰን ከአፋፍ ተመልሰን እናውቃለን። ጠላቶቻችን ገዝግዘው የጣሉን የመሰላቸው ግዜ ዳግም በሁለት እግራችን ቆመን እናውቃለን።

የእርስ በእርስ ግጭቱ፣ እርዛቱ፣ የውጪ ወራሪው የተፈጥሮ ቁጣው ብቻ በየዘርፉ ያልጎነተለን ጉዳይ ያልዳሰሰን መከራ አልነበረም። 50 እና 60 ዓመታትን መለስ ስንል እሁንም ድረስ ባለቀቀን የዘርና የጎጥ አባዜ ተፈትነናል። "ቀይ ሽብር" "ነጭ ሽብር" በሚል ተቧድነን ለቁጥር የሚታክቱ ዜጎቻችን ሕይወታቸውን አጥተዋል። እናቶች አልቅሰዋል። ሀገር ምሑራኖቿን፣ የማኅበረሰብ መሪዎችና ሽማግሌዎችን አጥታ ታላቅ ድብታ ውስጥ ገብታ ታውቃለች።

በ"ቸ" እና በ"ች" ሳይቀር ተጣልተናል። አርሶና ቆፍሮ የሚያበላን ገበሬ ለራሱ መቆም ሳያቅተው ለፖለቲካዊ ትርፍና ንግድ በነቀዙ የምዕራብ ሀገራት ፍልስፍና አስጨንቀውን እናውቃለን። እነዚህ ሁሉ ከጉድለቶቻችን ውስጥ የሚመደቡ፤ ከገጠሙን ወጣ ገባዎች ተርታ የሚሰለፉ ጥቁር ጠባሳዎቻችን ናቸው። ግን እንደ ሀገር አፈረሱን? እንደ ሕዝብስ አጠፉን? በፍፁም።

ዛሬስ? ዛሬም በመልካም ዕድሎች መካከል እንደቀደመው የታሪኮቻችን አካል ብዙ ጋሬጣዎች ከፊታችን ተደቅነዋል። አሁንም እንድንጎድል፣ እረፍት አልባ እንድንሆንና ስለ እድገታችን እንዳናማትር የሚጋርዱን መሰናክሎች በየጋቱ ተደንቅረዋል። አስተሳሰባችንን የሚፈትኑ፣ አንድነታችንን የሚጋርዱ፣ በፍቅርና በመተሳሰብ የሰከነ ሕይወት እንዳንመራ ሌት ተቀን ዕረፍት የሚነሱ አጀንዳዎች እዚህም እዚያም ተኮልኩለው ይታያሉ።

እንደ "ዘመነ መሳፍንት" በጎጥ ሸንነው በጎበዝ አለቆች ሊመሩን የሚሹ የውስጥ ሸረኞች ብቅ ብቅ እያሉ ነው። በማኅበረሰቡ ዘንድ የተሰመሩ ቀይ መስመሮችን ነፍስ እንደማያውቅ ጨቅላ የሚጎነታትሉም እንዲሁ በየስፍራው እንደትናንቱ ዛሬም አሉ። የውጪ ቀበኞቻችን የትናንቱን ጠንካራ ክርናችንን ዘንግተው በብዙ መልኩ ይፈታተኑናል።

አንድነታችን በፅኑ መሠረት ላይ የቆመና ጠንካራ "ኢትዮጵያ!" የሚል አለት የሆነች አገር የገነባን ቢሆንም በሕዝቦች መካከል ጠብን የሚጭሩ፣ የሀገር ምልክትና ባለውለታ የሆኑ ታላላቅ ተቋማትን ለመናድ አይናቸውን በጨው አጥበው ፍም እሳት ውስጥ እጃቸውን የሚከቱ ዛሬም እንደ ትናንቱ አልጠፉም።

ለዚህ ነው ትናንት የት ነበርን? ዛሬስ ምኑ ጋር እንገኛለን? ከታሪክስ ምን እንማራለን ብለን ለመጠየቅ የምንገደደው። የጠቃቀስናቸው ውጣውረድና ፈተናዎች በዘመን ዑደት ውስጥ ተከስተው ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊ መንፈስን የመበተን አቅም ከሌላቸው፤ የሺህ ዘመን ባሕል፣ ማንነት፣ ጠንካራ ሉዓላዊነትን የማነቃነቅ ኃይሉን ካላገኙ፤ ዛሬ ብልጭ ብለው ነገ ለሚከስሙ ነገር ግን እኛነታችንን ለማይለውጡ ፈተናዎች ስለምን እንበገራለን? ፤ስለምንስ እንርዳለን? ።

እንደቀደሙት አባቶቻችን በፈተና ቀን ፀንቶ መቆም፣ አንድ ሆኖ መገኘት፣ ኢትዮጵያዊ ማንነትና መልክን እንደ አለት ማጠናከር ከእኛ የሚጠበቅ የትውልዱ የቤት ሥራ መሆኑን እንገንዘብ። ታሪክ እራሱን ሲደግም እኛም የአባቶቻችን ልጆች መሆናችንን እናስመስክር። ሰላም!

> **እንዲያውም ዛሬ ሰቅዘው ለያዙንና እንፈታቸው ዘንድ ብልሃት ላጣንላቸው ስብራቶቻችን መፍትሔ እንደምናገኝ አያጠራጥርም። "በሽታውን ያወቀ መድኃኒት አያጣም" እንዲሉ ሕመሞቻችን ምን እንደሆኑ ዞር ስንል አቧራ የለበሱ የታሪክ ዶሴዎቻችን ይነግሩን ይሆናል። እኛ ግን ከትናንት ታሪኮቻችን ለመማር እንደ ማኅበረሰብ ምን ያህል ዝግጁ ነን?**

# ስፖርት

## የማይገታው የኢትዮጵያውያን አትሌቶች የዱባይ ማራቶን የበላይነት

ቦጋለ አበበ

በአለም አትሌቲክስ ትልቅ ትኩረት ከሚሰጣቸው አንዱ የሆነው የዱባይ ማራቶን በየአመቱ ሲካሄድ ሁሌም በውጤት ረገድ ተመሳሳይ ነው። ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ለእነሱ ብቻ የተዘጋጀ ውድድር እስኪመስል በዱባይ ማራቶን በሁለቱም ፆታ ሁሌም ፍፁም የበላይነት አላቸው። ይህ የበላይነት ደግሞ ቀዳሚዎቹን ደረጃዎች ይዞ በማጠናቀቅ ብቻ የተገደበ አይደለም። በሁለቱም ፆታ ከአንድ እስከ አስርና ከአንድ እስከ ሃያ በማጠናቀቅ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች ባለፉት በርካታ አመታት ፍፁም የበላይነት አላቸው። በዚህ ውድድር ሁሌም የየትኛው አገር አትሌት ያሸንፋል የሚለው ጉዳይ ሳይሆን የትኛው ኢትዮጵያዊ አትሌት ያሸንፋል ወይም ፈጣን ሰአት ያስመዘግባል የሚለው ጉዳይ ትኩረት ይስባል።

የዱባይ ማራቶን የኮቪድ-19 ወረርሽን ከተከሰተ ከ2019 በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ከትናንት በስቲያ ሲካሄድም በውጤት ረገድ የተለየ ታሪክ አልተፈጠረም። ለአመታት የዘለቀው የኢትዮጵያውያን አትሌቶች የዱባይ ማራቶን የበላይነት ለሃያ ሁለተኛ ጊዜ ባለፈው እሁድ ሲካሄድም በሁለቱም ፆታ ከአንድ እስከ አስር በማጠናቀቅ ቀጥሏል።

በዘንድሮው የዱባይ ማራቶን የታየ አንድ አዲስ ወይም የተለየ ነገር ቢኖር ውድድሩ በአንድ ቤተሰብ የበላይነት መጠናቀቁ ነው። ሃያ ሁለተኛውን የዱባይ ማራቶን በወንዶች የሃያ ሁለት አመቱ አትሌት አብዲሳ ቶላ በ2:05:42 ሰአት ሲያሸንፍ፣ በሴቶች ዴራ ዲዳ 2:21:11 በመግባት አሸናፊ ሆናለች።

ማራቶንን ለመጀመሪያ ጊዜ ሮጦ አሸናፊ የሆነው አብዲሳ ቶላ የወቅቱ የማራቶን የአለም ቻምፒዮኑ አትሌት ታምራት ቶላ ታናሽ ወንድም ሲሆን፣ በሴቶች መካከል የተካሄደውን ውድድር በበሳል ታክቲክ ከወሊድ ተመልሳ ማሸነፍ የቻለችው ዴራ ዲዳም የታምራት ቶላ ባለቤት ናት። ይህም በውድድሩ የታየ አንድ አዲስ ነገር ሆኖ በአለም መገናኛ ብዙሃን ተዘግቧል።

ወጣቱ አትሌት አብዲሳ ቶላ ከዘንድሮው የዱባይ ማራቶን በፊት አርባ ሁለት ኪሎ ሜትር ተወዳድሮ ባያውቅም በግማሽ ማራቶን 59:54 የሆነ የራሱ ፈጣን ሰአት አለው። በዚህም ዱባይ ላይ በማራቶን የተሻለ ልምድ ያላቸውን አትሌቶች በድንቅ የአጨራረስ ብቃት ለማሸነፍ አልከበደውም። ያምሆኖ ከታላቅ ወንድሙ የተሻለ ፈጣን ሰአት ማስመዝገብ አልቻለም። ታላቅ ወንድሙና የአለም የርቀቱ ቻምፒዮን ታምራት ቶላ በዱባይ ማራቶን እኤአ 2017 ላይ 2:04:11 በሆነ ሰአት ማሸነፉ ይታወቃል።



ኢትዮጵያኑ አትሌቶች ዴራ ዲዳና አብዲሳ ቶላ ከአንድ ቤተሰብ የ2023 የዱባይ ማራቶንን አሸንፈዋል፣

አዲሱን የዱባይ ማራቶን ቻምፒዮን ተከትሎ ሌላኛው ኢትዮጵያዊ አትሌት ደሬሳ ኡልፋታ 2:05:51 በሆነ ሰአት ሁለተኛ ሆኖ ሲያጠናቅቅ ያስመዘገበው ሰአት በርቀቱ የግሉ ፈጣን ሰአት መሆን ችሏል። 2:05:58 በማጠናቀቅ አስደናቂ ፉክክር ያደረገው አትሌት ሃይማኖት አለው በሰባት ማይክሮ ሰከንዶች ብቻ ተቀድሞ ሶስተኛ ደረጃን መያዝ ችሏል።

በድንቅ የታክቲክ ፍልሚያ የታጀበው የሴቶች ውድድር አሸናፊ የሆነችው ዴራ ዲዳ ባለፉት ሶስት የማራቶን ውድድሮቿ ከ2:21:45 የፈጠነ ሰአት ርቀቱን ማጠናቀቅ አልቻለችም ነበር። በነዚያ ውድድሮቿ ከአምስተኛ ደረጃ የተሻለ ውጤት ይዛ ማጠናቀቅም አልቻለችም ነበር። እንደ ቤተሰብ ውጤታማ በሆኑበት የዘንድሮ የዱባይ ማራቶን ግን ከወሊድ ተመልሳ ቀዳሚ ሆና ከማጠናቀቅ ባለፈ ያስመዘገበችው ሰአትም በርቀቱ የግሏ ምርጥ ሰአት ሆኖ ሊመዘገብላት ችሏል።

ቀዳሚ ሆና ያጠናቀቀችው ዴራን ተከትላ የ2019 ቶኪዮ ማራቶን ቻምፒዮኗ አትሌት ሩቲ አጋ 2:21:24 በሆነ ሰአት ሁለተኛ ሆና ስታጠናቅቅ አትሌት ስራነሽ ይርጋ 2:21:59 በሆነ ሰአት ሶስተኛ ደረጃን ይዛ ውድድሩን ፈጽማለች።

ባለ ድሉ አትሌት አብዲሳ ቶላ ከውድድሩ መጠናቀቅ በኋላ ለመገናኛ ብዙሃን አስተያየቱን ሲሰጥ " ለዚህ ውድድር በደንብ ተዘጋጅቻለሁ፣ እንዳሸንፍ የረዳኝም ይሄው ምክኒያት ነው፣ በውድድሩ ወቅት የነበረው የአየር ጸባይ ጥሩ ቢሆንም መጠነኛ ወበቅ ነበር፣ ለዚህም ቢሆን ጥሩ ተዘጋጅቼ ቀሪውን ስራ ለፈጣሪ ሰጥቼ ነበር" በማለት ተናግሯል።

የሴቶቹ ባለድል አትሌት ዴራ በበኩሏ፣ "በጥሩ ፉክክር የታጀበ አስደናቂ ውድድር ነበር፣ እኔም እዚህ የተገኘሁት ለማሸነፍ ነው፣ ውድድሩ በታክቲክ ፉክክር የጠነከረ ቢሆንም ፈጣሪ ረድቶኛል፣ ይህን ውድድር እንደማሸንፍ በራስመተማመን ነበረኝ ይህም ባለድል ለመሆን ጠቅሞኛል" በማለት አስተያየቷን ሰጥታለች።


### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

1. የአመልካች ስም YBY AG አድራሻው Gewerbestrasse 10, 6330 Cham, Switzerland
2. የማመልከቻ ቁጥር እና ማልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን -FTM/13802/2022 ፤ 05/10/2022
3. የንግድ ምልክቱ፡- የቃል
4. ምልክት እና ቀለም ዓይነት፡- ጥቁር እና ነጭ

**YBY**

5. ዓለም አቀፍ ምድብ ፡- 32 እና 33
6. የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች፡-

ምድብ 32፡- አልኮል ያልሆኑ መጠጦች፤ አልኮል ያልሆኑ ወይኖች እና፤ አልኮል ያልሆነ የሚያብረቀርቅ ወይን።

ምድብ 33፡- የአልኮል መጠጦች ከቢራዎች ውጭ፤ ወይን፤ የሚያብረቀርቅ ወይን።

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል። ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት መመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ካልቀረበ ምልክቱን የምንዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን። ስለሆነም ማንኛም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ካለባለቤቱ ፈቃድ ውጪ በዚህ ምልክት የሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በህግ ክስ ይመሰረትበታል።

**ኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXII No-157 7/6/2015 (14/2/2023)**

### የባለቤትነት ስያሜ እና የአድራሻ ለውጥ

በኢትዮጵያ ውስጥ FTM/6733/15 አለም አቀፍ ምድብ 36 የተመዘገበ የሚከተለው ንግድ ምልክት፡-

**ROTHSCHILD & CO**


የባለቤት ስያሜ እና የአድራሻ ለውጥ ከ Rothschilds Continuation Holdings AG አድራሻው Baarerstr. 95, 6301 Zug, Switzerland ወደ Rothschild & Co Continuation Holdings AG አድራሻው Baarerstrasse 95, Zug, 6300, Switzerland እንደተለወጠ በዚህ ማስታወቂያ ያሳውቃል። ስለዚህ ይህንን ለውጥ እንዲያስተውሉ በትህትና እንጠይቃለን።

**የኢትዮያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXII No-157 7/6/2015 (14/2/2023)**

### የንግድ ምልክት ምዝገባ ተቃውሞ ጥሪ ማስታወቂያ

1. የአመልካች ስም Merck Sharp & Dohme B.V. አድራሻው Waarderweg 39 2031 BN, Haarlem, The Netherlands
2. የማመልከቻ ቁጥር: FTM/13097/2022 ማልከቻው ገቢ የሆነበት ቀን 30/09/2021
3. የንግድ ምልክቱ፡- የምስል
4. ምልክት እና ቀለም ዓይነት፡- ብርቱካንማ
5. የብቸኝነት መብትን ስላለመጠየቅ: capsule only
6. ዓለም አቀፍ ምድብ ፡- 05
7. የሚሸፍናቸው ምርቶች ወይም አገልግሎቶች፡





ምድብ 05፡- የመዳሃኒት ዝግጅቶች እና ንጥረ-ነገሮች፤ ከላይ ከተጠቀሱት እቃዎች ውስጥ ለምርመራ አገልግሎት።

አመልካች ከላይ የተመለከተውን የንግድ ምልክት ለማስመዝገብ ጥያቄ አቅርበዋል። ስለሆነም ተቃዋሚ ካለ የጋዜጣ ማስታወቂያው በወጣ በ60 ቀናት ውስጥ የተጠቀሰው የንግድ ምልክት መመዝገብ እንዳይገባ የሚያስችል ማስረጃ ለኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን ካልቀረበ ምልክቱን የምንመዘግብ መሆኑን እናስታውቃለን። ስለሆነም ማንኛም ግለሰብ ወይም የህግ ሰውነት ያለው ተቋም ካለባለቤቱ ፈቃድ ውጪ በዚህ ምልክት የሚጠቀም ወይም አስመስሎ በሚሰራ ላይ በህግ ክስ ይመሰረትበታል።

**ኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXII No-157 7/6/2015 (14/2/2023)**

### የንግድ ምልክት እድሳት ማስታወቂያ

| | | |
|---|---|---|
| 1. | የንግድ ምልክት ባለቤት ስም | ፒቲሲናር ኣንትጆል<br>Jl Malak II No 1-3 (C/0. Jl Orpa No.1-3) Roa Malaka, Tamobora Jakarta Barat |
| 2 | የማመልከቻ ቁጥር | FTM/6910/15 |
| 3. | የንግድ ምልክት |  |
| 4. | ባለቤቱ ን/ምልክቱን የሚጠቀምበት | 2/2/2005ዓ.ም Vol. LXXII-N0.032 አዲስ ዘመን ላይ በወው ማስታወቂያ ላይ ለተዘዘረዘሩት ዕቃዎችና አ7ልግሎቶች ነው። |
| 5. | የንግድ ምልክቱ እ.ኤ.አ. | ከ30/11/2022 እ.ኤ.አ 30/11/2029 እ.ኤ.አ ታድሷል።<br>በሆኑም ማንኛውም ሰው ከባለቤቱ ፍቃድ በዚህ የንግድ ምልክት ከተጠቀ በኢትዮጵያ ህግ ይጠየቃል። |



**የኢትዮጵያ አእምሯዊ ንብረት ባለስልጣን**

**ADDIS ZEMEN VOl-LXXXII No-157 7/6/2015 (14/2/2023)**